ምዕራፍ ሀያ

የከተማው ዋና ዋና መንገዶች በዩኒቨርስቲው ተማሪዎች መወረር ጀምረዋል ። የአራት ኪሎና አካባቢዋ ቡና ቤት አሳላፊዎች ፣ ለተማሪ ሻይ — ቡና በማቅረብ ተዋክበዋል ። የተማሪዉ አንሶላዎች ፣ ልብሶችና በየሥርቻው ተወርውረው የከረሙ የእግር ሹራቦች ከውሃ በመታረቅ ላይ ናቸው ። ሐሜት ፣ ውረፋ ፣ ዘለፋና ቀልድ ጊዜአቸውን ጠብቀው ተመልሰዋል ። በሴሚስተሩ ውስጥ በዩኒቨርስቲዉ የተደረገች እንዳች ነገር ሳትቀር እየተነሣች መብጠልጠያዋ ጊዜ ነው ።

ይህ ሁሉ፣ ፈተና ማለቁን የሚያበሥር ነው ። የፈተናዉ ውጤት ቀርቦ ፣ ማዕበሉ ማንን ጠርጎ ፣ ማንን እንደ ተወ እስኪታወቅ ድረስ ለሁለት ሳምንቱ የዕረፍት ቀናት አብዛኛው ተማሪ ከዚህ ክልል አይወጣም ።

አቤልና እስክንድርም የመጨረሻውን ፈተና እንደ ተፈተኑ ግቢውን ለቀው ወጥተዋል ። የተዝረከረኩ ዕቃዎች ለማስተካከል እንኳ ፣ ወደ መኝታ ክፍላቸው አልተመለሱም ። ተያይዘው በቀጥታ ወደ እስክንድር እናት ቤት ተክለ ሃይማኖት አካባቢ ሔዱ ። አቤል ለዐውደ ዓመትና ዐልፎ ዐልፎም ለዕረፍት እነ እስክንድር ቤት መሔድ የጀመረው ገና፣ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሳለ ከእስክንድር ጋር እንደ ተዋወቁ ነው ። አንዳንዴ አብረው ይሔዱና የተገኘውን ቀማምሰው ተጫውተው ይመለሳሉ ። ዘንድሮ ግን አቤል ቤታቸው ሳይሔድ ቆይቷል ።

“ የጠፋው ሰው ! እንደ ምን አላችሁ ፣ ልጆቼ ?’ አሉና እናትየዋ ፣ ሁለቱንም አቅፈው ሳሙዋቸው ።

“ አቤል ፣ ምነው እንዲህ ጠፋህ ልጄ ? ”
“ ምን እባክዎን ፣ ጥናት በዝቶ ኮ ነው ። ”

“ ቢሆንስ ታዲያ ፣ አንዳንዴ መቼስ እናት ቤት ብቅ ትብሎ የተገኘውን ቀማምሶ ይኬዳል ። አሁን ፈተና ጨረሳችሁ ፣ አይደለም ? ”

“ አዎ መቼስ ። ”

“ እንግዲህ አንድ ፈተና ነዋ የቀራችሁ ? የፈታችን ሰኔ መመረቂያችሁ አይደለም ? ”

አቤል ዝም አለ ። እስክንድር ስሜቱ ስለ ገባው ቶሎ ብሎ ጣልቃ ገባ ።

“ አዎ ፣ አይዞሽ ደርሰናል ” አላቸው ። እጁ ላይ ሲጋራ መኖሩን ያዩት ይሄኔ ነበር ።

“ ይሄንን ሲጋራህን ምናለ ብትተው እስክንድር ? አቤል ፣ ጓደኛህን አትመክረውም ? ! ”

ብዙ ዓመት የተናገሩት ነገር ነው ። ሆኖም ዐይናቸው ባየ ቁጥር ዝም ማለት አይችሉም ። አቤል ከመቅለስለስ ሌላ ምንም አልመለሰም ።

“ አይዞሽ ፣ በቅርቡ አቆማለሁ ” አላቸው እስክንድር ራሱ ። እሳቸው ማቄ — ሁሉም የሚላቸው ነገር ስለሆነ ።

“ ማዘር ሙች አቆማለሁ ። ለአራት ወር ያህል ታገሺን ብቻ ” አላቸው ።

ከልቡ ለማቆም ቆርጦ ነበር ። እናትየው ግን ጊዜው ደርሶ እስካላዩ ድረስ ሊያምኑት አይችሉም ።

ምግብ አቀረቡላቸውና ከበላሉ በኋላ፣ሲጫወቱ ቆይተው ሲመሻሽ እስክንድርና አቤል ሊሔዱ ሲሉ ፡—

“ ዛሬ ለምን ከዚሁ ስትጫወቱ አታድሩም ? ” አሉ እናትየዋ ።

“ አአይ እንሔዳለን ። እዚያው ካምፓችን ይሻለናል ” አለ እስክንድር፣እሳቸው በሚናገሩት ዐይነት ።

እስክንድር በዕረፍቱ ሰሞን አቤልን ጥሎ ቤቱ መክረም አልፈለገም ። አብረው እንዳይሆኑ ደግሞ ቤቱ አይመችም ።

ሁለት መኝታ ብቻ ነው ያለው ። አንዱ የናትየዋ ነው ። በአንዱ መኝታ ላይ ከታናሽ ወንድሙ ጋር ሦስት ሆነው ተጨናንቀው መክረሙን አልፈለገም ። በዚያ ላይ እናትየዋ ለእነሱ የሚያቀርቡትን ምግብ ጣፈጠ አልጣፈጠልኝ ብለው ሲጨነቁ እንዲከርሙ አይፈልግም ። ከአሁን በፊትም ቢሆን ትልቁ የክረምት ዕረፍት ላይ ካልሆነ ፣ የገናውን ዕረፍት ቤቱ አሳልፎ አያውቅም ። እዚያው ዩኒቨርስቲ ውስጥ ነው የሚከርመው ። እናትየውም ይህንኑ ስለሚያውቁ ብዙም አላግደረደሩት ።

ተሰናብተዋቸው ከውጭው በር እንደ ደረሱ፣እናትየው እስክንድርን ወደ ኋላ አስቀሩትና አንድ ነገር እጁ ውስጥ ሽጉጥ አደረጉለት ።

“ ምንድነው እሱ ? ” አላቸው ፣ ምን እንደሆነ ልቡ እያወቀ ።

“ ያዘው ለዚያ ለምናምንቴ ለሱስህ ይሆንሃል ” አሉት ። የዐሥር ብር ኖት ነበር ።

“ እኔ ከሌላ ቦታ አላጣም እባክሽ ። ይሄ ለራስሽ ይሁንሽ ” አላቸው ። ለማግደርደር ያህል ሳይሆን ከልቡ ነበር ። ምን ጊዜም ከእናቱ ገንዘብ ሲወስድ ልቡ ያዝናል ። እንደ ሲጋራ ሱሰኝነቱ አይቅበዘበዝም ።

“ ያዘው ግድ የለህም ። እኔ አለኝ ። አንድ ዐርባ ብር የመንደር ዕቁብ ነበረችኝ ፤ እሷ ወጥታልኝ ነው ” አሉት ።

አመስግኖ ብሯን ኪሱ ከተተ ። ወዲያው ግርታ በሐሳቡ መጣችበት ። ግን በዐሥር ብር ምን ሊኮን ?

“ አቤል ፣ በል እንግዲህ ብቅ እያላችሁ ጠይቁኝ ። አሁን ዕረፍት ናችሁ ” አሉት እናትየዋ ፣ አቤልን ቅር እንዳይለው ።

ከእናቱ ተለይተው ከሔዱ በኋላ፣እስክንድር ስለ ድህነትና የእናት አንጀት ተቃራኒ ሁኔታ እያብሰለሰለ ነበር ፣ ድህነት እጅዋን ሊያስራት ይሞክራል ፤ እናት እጅዋን ለልጅዋ ለመዘርጋት ትፍጨረጨራለች ። ምኞቷና አድራጎቷ እኩል አይሆንም ። በፍቅር ወደ ልጅዋ ስትንጠራራ

ድህነት ጨምድዶ ይይዛታል ። ግን ያም ሆኖ አትረታም ። አትሸነፍም ። እንደ ምንም ተፍጨርጭራ የልጅዋን እጅ ትንካለች ። ”

“ አሁን ወዴት ነን ?” አለ አቤል ፣ ትንሽ እንደ ተጓዙ ።

“ አንድ ቤት ጎራ ብለን ደርቆ የከረመ ጉሮሮአችንን እናርጥብ እንጂ ! ” አለ እስክንድር ።

አቤል ገንዘብ መቆጠብ የማይችለው የእስክንድር እጅ አስገርሞት ሳቀ ። ከእናቱ የተቀበላትን ገንዘብ ለማጥፋት እንደ ቸኮለ ገባው ።

“ ይልቅ ቦታ ምረጥ ። የት ይሻለናል ? ” አለው እስክንድር ።

“ ወደ ሠፈራችን አቅራቢያ አይሻልም ? ” አለ አቤል ፣ መቼም ከዩኒቨርስቲው አካባቢ ርቆ መቆየት አይሆንለትምና።

“ ስድስት ኪሎ ደኅና ቡና ቤት የለማ ! ከጠግን አይቀር ትንሽ ትርምስ ብጤ ያለበት ይሻለናል ። የጠርሙስ ካካታ ! ”

“ አራት ኪሎ እንሒዳ ! በዚያው ወደ ካምፓስ ለመግባት ይቀርበናል ። ”

በዚሁ ተስማምተው ወደ አራት ኪሎ አመሩ ።

እዚያ ሲደርሱ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ገደማ ሆኖ ነበር።እስክንድር ቻቻታ ያለበትን ቦታ ለመምረጥ ስለ ፈለገ፣ ከቡና ቤት ቡና ቤት ሲዘዋወሩ፣ በብዛት የሚያጋጥማቸው የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበር ። ተማሪው ታስሮ የተፈታ ሆኖ አል ። ባንኮኒ ተደግፎ የሚጠጣው ፣ የሴት አሳሳፊዎችን ዳሌ የሚዳብሰው ፣ በቡድን ተቀምጦ እየጠጣ የሚንቻቻው ተሜ ነው ። ከወላጅ ከዘመድ የተላከ ፣ ከወዲያ ወዲህ ተጠራቅሞ ተቀብሮ የቆየ ገንዘብ መውጫው ዕለት ነው ። በፈተና ማግሥት ስክሮ መጥቶ ግቢው ውስጥ መደንፋት ፣ የማይጠጡ ተማሪዎችን መረበሽ ። ወይም ሰክሮ በየበረንዳው አድሮ ጠዋት “ ጅብድ ” አርጎ ማውራት በዩኒቨርስቲው ውስጥ እየተለመደ የመጣ ይመስላል ። በተለይ ይህ ሁኔታ አይሎ

የሚታየው ፣ ከገጠር በመጡ ተማሪዎች ላይ ነው ። የአዲስ አበባው ተማሪ የቡና ቤቱን ትርምስ ከማዘውተር “ የኖርን በት ነው ” በማለት ዐይነት ቆጠብ ይላል ። ገንዘቡንም ቢሆን ከገጠር እንደ መጡት አጠራቅሞ ማቆየት አይችልም ። አንዳንዱ እንደ ቱሪስት አስጎብኝ ገጠሬዎቹን ይዞ የከተማውን ምርጥ ቡና ቤቶች በማስተዋወቅ የጋራ “ ጀብድ ” ይፈጽማል ።

እነ እስክንድር አንድ ሞቅ ያለ ቡና ቤት አግኝተው ገቡ ። አንድ አንድ ቢራ ይዘው ቁጭ ከማለታቸው ፣ ሳምሶን ጉልቤው ዝንጥ ብሎ መጣ ። ሁሉም አራት ኪሎ መጠጣት የመረጡት ማታ ወደ መኝታ ቤታቸው ለመግባት እንዲቀርባቸው ይመስላል ።

ሳምሶን እስክንድርና አቤልን ሲያገኛቸው ደስ አለው ። በተለይ አቤልን መጋበዝ ይፈልግ ነበር ። ጠዋት የለበሰውን ቀያይሮ አፍላ ጉልበቱን ወጣጥሮ በሚያሳይሙሉ ጅንስ ሽክ ብሎአል ።

“ ከመቼው ተሠየማችሁ ? ” አላቸው ፣ አጠገባቸው ለመቀመጥ ወንበር እየሳበ ።

“ አንተም ደኅና ጊዜ ደርሰሃል ፤ ቁጭ በል ” አለው እስክንድር ።

ሳምሶንም ቢራ አዝዞ ተቀመጠ ። አቤል ገና በአንድ ቢራ መፍዘዝ ጀምሮአል ። ዝምታው እንግዳ ነገር ባይሆንም ፣ ከዚያ በላይ ጥልቅ ተመስጦ ውስጥ እንደ ገባ ያስታውቅ ነበር ። በአዳራሹ ውስጥ የሚንቻቻውን ጠጪ ትክ ብሎ ይመለከታል ። ዐይኑ ይመልከት እንጂ ልቡ ከዚያ አልነበረም ።

እስክንድርና ሳምሶን ፣ ቢራ እስኪደግሙ ድረስ ምላሳቸው አልተፍታታም ። ሆኖም የአቤል ሁኔታ በግምት ስለ ገባቸው ከተመስጦው ሊያነቃቁት ሞከሩ ።

“ አቤል ፣ ተጫወት እንጂ ! ” አለው ሳምሶን ፣ ፍቅር ባዘለ ለስላሳ ድምፅ ። ሳምሶን ከማንም ጋር በሰላም እንኳ ቢነጋገር ፣ የድምፁ ቅላጼ ቁጣ ያለበት ይመስላል ። አቤል ላይ ሲሆን ምን እንደሚያላላው ለራሱም ይገርመዋል ።

“ እሺ ፣ ጨዋታ አምጣ በል ” አለ አቤል ፣ ስሜቱን ወደ እነሱ ለመሰብሰብ እየሞከረ ።

“ ድብርትን ለምን ይዘሽው አልመጣህም ? ” ሲል እስክንድር በድንገት ሳምሶንን ጠየቀው ። ጨዋታ ለመክፈትም ከሳምሶን ጋር ለመለካከፍም ያቀረበው ጥያቄ ነበር ።

“ እሺ አይለኝም እንጂ ይዤው እመጣ ነበር ” አለ ሳምሶን ከልቡ ፤ መኝታ ክፍል ውስጥ ቢለክፈውም ቅሉ ፣ በሳምሶን ልብ ውስጥ የመረረ ተንኮል ወይም መጥፎ ስሜት አልነበረም ።

“ ሆሆይ ! ኧረ እሱ አንገቱን ቢያርዱትም ከሰው ጋር አይወጣም ” አለ አቤል ፣ ጸባዩን ስለሚያውቅ ።

ስለ ድብርት ከሳምሶን የበለጠ የሚያውቁት ብዙ ጊዜ አብረውት የኖሩት አቤልና እስክንድር ናቸው ። ሦስት ዓመት ያህል አንድ መኝታ ቤት ውስጥ ሲኖሩ ፣ አንዳችም ከድብርት ጋር የሚጋሩት ትውስት የለም ። ከግቢው አይወጣም ። ከወጣም ብቻውን ነው ። ከሰው ጋር ተቀራርቦ ተጫውቶ የሚጣጣም አይመስለውም ። የእሱ ሕይወት እንቅልፍን ትመስላለች ። የሕይወትነት መዓዛ የላትም ። በዚሁ ምክንያት እስክንድርን ድብርት ፣ ከውስጡ ወይም ከውጭው አካሉ አንድ የተደበቀ የጎደለው ክፍል ይኖራል የሚል ጥርጣሬ አለው ።

“ እኔ ማየት የምጓጓው እሱ የሚይዛትን የሴት ጓደኛ ነው ” አለ እስክንድር ።

“ እንዴት ፣ የእሱ ብጤ ድብርት አለችው ’ኮ ! ” አለ ሳምሶን ፣ “ ብዙ ቀን ግቢው ውስጥ አብረው አይቻቸዋለሁ ። ”

“ እኛ ግቢ ውስጥ ? ” አለ እስክንድር ተደንቆ ።

“ ስነግርህ ! ” አለው ሳምሶን ፣ “ እንዲያውም ድብርት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሥቅ ያየሁት ከእሷ ጋር ሆኖ ነው ። ወሬአቸው ሁሉ በሹክሹክታ ዐይነት ፣ አለ አይደል ፣ ብቻ በዐይንህ ብታያቸው ፍቅር መሆኑ ይገባሃል ። ”

“ እንዲያው ምን ምን ይላት ይሆን ? እኔ እሱ ለሴት ልጅ የሚያወራውን ነገር ለመስማት እጓጓለሁ ። ግን አንተ ባልከው ዐይነት አገጣጥሞኝ አያውቅም ። ”

“ እጅሬ ምኑ ሞኝ ነው ላንተ የሚታየው ? ! እሷን ሲያገኛት ቦታው ጭር የሚልበትን ጊዜ ጠብቆ ነው ። ”

‘ ወይ ጉድ ! መቼም ፍቅር የማያሸንፈው ልብ የለም ’ አለ እስክንድር በልቡ ። ስለ ድብርት የበለጠ ለማወቅ ጓጉቶ ነበር ። ሆኖም ጨዋታው በተዘዋዋሪም ቢሆን ፣ አንዳንድ የአቤልን ድርጊቶች እንደሚነካ ስለ ገመተ አርዕስቱን ለመለወጥ ፈለገ ። ሳምሶንም ይህንን ሁሉ ልብ ሳይል እንደ መጣለት ነበር የሚጫወተው ። እስክንድር ግን የአቤል ስሜት እየተለዋወጠ እንደ መጣ በሥርቆት ከገጽታው ላይ አንብቦአል ። ድብርት የሴት ጓደኛውን ለማግኘት ጭር ያለ ጊዜ መጠበቁ የአቤልን ስሜት ክፉኛ ነክቶታል ። እሱም ትዕግሥትን ለማየት የሚጠቀምባቸውን ጊዜያቶች ያውቃል ።

“ ስማኝ ሳምሶን ! ግን ለምንድነው አንተ ብዙ ጊዜ ድብርትን የምትለክፈው ? ” በማለት እስክንድር አርዕስቱን አሸጋገረው ።

“ ለተንኮል አይደለም ። ግን የሚነፋነፍ ሰው መልከፍ እንዲሁ ደስ ይለኛል ። እንዴት ብዬ ላስረዳህ ? ለምሳሌ ፣ ቀርቦ መናከስ የማይደፍር ውሻ በሩቁ እያፈገፈገ ሲጮህብህ እልሁን ለማስጨረስ በዱላ እንደምትተናኮለው ዐይነት ነው ። ብቻ እንዲሁ ስለክፈው ደስ ይለኛል እንጂ ለድብርት መጥፎ አመለካከት የለኝም ። ለየት ያለ ተፈጥሮ ስላለው ያስገርመኛል ” አለና ፣ አሳላፊዋን ለመጥራት ጠረጴዛውን ጠበጠበ ።

“ አቤት ! ምን ልታዘዝ ? ” እያለች አንገቷ በንቅሳት የተዥጎረጎረ ሴት ከፊታቸው መጥታ ቆመች ።

“ ቢራ ድገሚን — ሦስት ቢራ ! ” አላት ሳምሶን ፣ በዚያው ቁጡ ድምፁ ።

“ እኔ ይብቃኝ ! ” አለ አቤል ።

“አትቀልድ እባክህ ። አንቺ እኔ የማዝሽን አምጪ ! ” አለና ሳምሶን አሳላፊዋ ላይ ጮኸባት ።

‘ ጥርስሽን እንዳያወልቅ ’ አለና እስክንድር በልቡ ሣቀ ።

“ እኔኮ ያንተም ተፈጥሮ ያስገርመኛል ” አለው እስ ክንድር - ሳምሶንን ።

“ እንዴት ? ”

“ አሁን ሚስተር ሆርስ ከአቤል ጋር ከታረቀ በኋላ ለምን ትዝትበታለህ ? ”

“ አዎ ! የማታውቀው ነገር አለ ፣ እስክንድር ። እየዛ ትክ የምትተው ከሆነ ዛቻው ሲደጋገም ሰው ይንቅሃል ። ወንድ ከሆንክ አንዴ ማቅመስ አለብህ ። እንዲያውም አን ተን ብዬ ነው እንጂ ፣ እሱን ልጅ አንድ ቀን ብሰብረው ደስ ይለ ኛል ። ከፈለገ የገዛ ጥርሱን ከመሬት አሰለቅመዋለሁ ። ”

“ጡንቻህን ፈትነኝ እያለ ያስቸግርሃል መሰለኝ” አለና እስክንድር እየሣቀ ከእሱ መልስ ሳይጠብቅ ፣ “ ብቻ ያለን በትንም ጊዜ አትዘንጋ ፣ ሀያኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነን ” አለው ።

“ እና ? ” የብሽቀት ድምፅ ነበር ።

“ እናማ ስፖርተኝነትህን እወድልሃለሁ ። ይህችን በጡንቻ መመካትህን ግን . . . ”

“ እንግዲህ አትልከፈኝ ፣ ልጠጣበት ! ” አለና ቢራ ውን ተጎነጨ ።

ሳምሶን ሌላ ሰው እንዲህ ቢናገረውም ፣ ካልተደባደበ በዋዛ አይላቀቁም ነበር ። ለእስክንድር ያለው ክብር ግን ብዙ ዓመት ከቆየ የልጅነት የአስተሳሰብ ተጽዕኖ የመጣ ነው ። የሠፈር ልጆች እንደ መሆናቸው መጠን ፣ ሳምሶን ስለ እስክንድር ብዙ ነገር ያውቃል ። እሱ ገና ልጅነቱን ሳይ ጨርስ እስክንድር በሠፈራቸው ውስጥ ስመ - ጥር ጎፈምሳ ነበር ። እንዲህ እንዳሁኑ ከመስከኑ በፊት እናቱ በእስክንድር

ያላዩት አበሳ የለም ። ከለውጡ በፊት ጾብ አሸትቶ ነበር የሚፈልገው ። እስር ቤትን ቤቱ አድርጎት ነበር ። አንዴ ጾበኞቹ በቡድን ሆነው ከደበደቡት በኋላ ፣ ሆዱ ላይ በጩቤ ወግተውት ለጥቂት ነው ከሞት የተረፈው ። ከለውጡ በኋላ ደግሞ በወቅቱ በተፈጠሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ሳቢያ ያልቀመሰው አበሳ የለም ። ችኩል ነበር ። ሰው አይገራ ውም ፤ ያየሁት አይለፈኝ የሚል ስሜት ያሸንፈዋል ። የጀብደኝነት ስሜት ያጠቃዋል ። ትኩስ ኃይልነቱ መንፈሱን ያቅበጠብጠዋል ። አሁን ግን በዕድሜም በብስለትም ሰክኖ ፣ እንኳን ለራሱ ሌሎችን ይመክራል ። ከአፍላነት ቅብጥብጥ ጊዜው ይዞ የመጣውና አሁንም ያልተወው ነገር ቢኖር የሲጋራ ሱስ ብቻ ነው ። ይህ ሁሉ ሁኔታ በሳምሶን ላይ የሚ ኖረው ተጽዕኖ ቀላል አይሆንም ። በጸጉሩ ኪንኪነት እየለከ ፈው ከእስክንድር ጋር መቃለድ የጀመረው እንኳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው ።

“ አቤል ፣ እባክህ አንተ ተጫወት ፤ ይሄንን ተወው ” አለ ሳምሶን እስክንድርን በመንቀፍ ዐይነት ።

“ እየሰማኋችሁ ‘ኮ ነው ” አለ አቤል ፣ በጨዋታ ቸው ውስጥ የቆየ ለመምሰል ጥርሱን በውሸት ብልጭ እያደረገ ።

ሐሳቡ በከፊል ወደ እንትዕግሥት ዘምቶ ነበር ። ፈተና ከጨረሰች በኋላ ፣ ወዴት ትሔድ ይሆን ? ዐርፋ መተኛት ወይስ ዙረት መውጣት ? እያለ ሲያሰላስል ነው የቆየው ። ሁለተ ኛውን ጠርሙስ ቢራ ግማሽ አድርሶታል ። ከቻቻታው ጋር ቢራው ሞቅ አድርጎት ውስጥ ውስጡን እየሰከረ መምጣቱ ይሰማው ነበር ። የመጠጣት ልምድ ስለ ሌለው ፣ ጭንቅላቱ ቶሎ መረታት ጀምሯል ። ድፍረትም ተሰማው - ማንንም ያለመፍራት ዐይነት ስሜት !

“ ለምን ሙዚቃውን አይቀይሩልንም ? ” ሲል ድምፁን አሰማ ። የእንግሊዝኛ ሙዚቃ ነበር - አዳራሹን የሚነቀ ንቀው ፤ “ ማስቀየር እንችላለን ። የማን ክር ይደረግ ? ” አሉ እስክንድርና ሳምሶን በአንድ ድምፅ ። አቤል ከዝምታ ወደ ተሳትፎ መምጣቱ ደስ አሰኝቶአቸው ነበር ።

“ . . . የ . . . የ . . . የመልካሙ ተበጀ ክር ቢሆን ይሻላል ” አለ አቤል በተሰባበረ ድምፅ ።

እስክንድርም ሆነ ሳምሶን በፍጥነት የጠረጠሩት ነገር አልነበረም ። አሳላፊዋን ጠርተው ክሩ እንዲቀየር አዘዝዋት።

“ ባለቤትየዋ እሷ የመረጠችው ዘፈን ካልሆነ እሺ አትልም ፤ ግን ልሞክርላችሁ ” አለች አሳላፊዋ ።

“ ንገሪያት ! ለምን እሺ አትልም ! ” አለና ሳምሶን አፈጠጠባት ።

እሷ ዘፈኑን ልታዝዝ ስትሔድ አቤል ቀድሞ በልቡ ያንጐራጉር ጀመር ።

“ ኧረ ሙላ ምቱ ወዳጅ ዘመዶቼ
ዐይናፋር ሆኛለሁ ፣ ዐይናፋር አይቼ
ሰላምታ አልሰጠኋት — አላነጋገርኳት
በዐይን ብቻ እያየሁ አንድ ዓመት ወደድኳት ። ”

ልቡ ይህን እያዜመ፣ ጆሮው የሚሰማው ግን ሌላ ሙዚቃ ነበር ። ቢጠብቅ ፣ ቢጠብቅ የተለወጠ ነገር የለም ። ጥቂት ቆይታ አሳላፊዋ ተመልሳ መጣች ።

“ የመልካሙ ክር የለም ብላለች ፣ ባለቤትየዋ ! ”

አቤል በሽቆ “ ገደል ግቢ በያት ! ” ከማለቱ ዐይኑ እንባ አቀረረ ። የሰው ስሜት የማይጠበቅበት ዓለም ! ባለቡና ቤቶች ፍቅረኛውን የሚያስታውስበትን ዘፈን አይከፍቱለትም ። መምህራን ትምህርት ምን ያህል እንዳስጠላው አይረዱለትም ። ወላጆቹ ልጃቸው ከድህነት ቀንበር እንዲያላቅቃቸው ይመኛሉ እንጂ ፣ እሱ ያለበትን ችግር አያውቁለትም ። ጓደኞቹ ብቸኝነቱን አይፈቅዱለትም ።

“ እሷ ከሙዚቃዋ ጋር ገደል ትግባ ! አንቺ ቢራ ድገሚን ” አላት ሳምሶን በሽቆ ።

“ ኧረ ይብቃን ! ሰዓቱም መሽቷል ፣ የካምፓስ ፖሊሶች አያስገቡንም ” አለ እስክንድር ፣ ኪሱን እየዳበሰ ።

“ አምጪልን እባክሽ እንጠጣው ! ዛሬ ካምፓስ ማን ይገባል ? ” አለ ሳምሶን ፣ በሞቅታ ስሜት ።

“ በይ እንግዲያው አንቺንም እንጋብዝሽ ፣ የምትጠጪውን ነገር ይዘሽ ነይ ” አላትና እስክንድር ፣ ወደ ሳምሶን ዘወር ብሎ ፣ “ ከጠጣን አይቀር መሐላችን አንዲት አንስታይ ስትኖር ይሻላል ” አለው ። ከሳምሶን ሁኔታ ገንዘብ እንደያዘ ገምቶ ነበር ።

አቤል ምንም አስተያየት አልሰጠም ። የያዘውን ቢራም አልጨረሰም ። ከዚያ በላይ መጠጣት አልፈለገም ። ሆኖም አልተከላከለም ። ሕይወትን የመሰላቸት ዐይነት ነበር - የሚሰማው ። ለምንም ነገር ያለመጨነቅ ። ስካር ማለት ይሄ ይሆን እንዴ ? ስለ መጠጣት፣ ስላለመጠጣት ፣ ካምፓስ ስለ መግባት፣ ስላለመግባቱ አቤል ደንታ የለውም ። ‘ እነሱው ይከራከሩበት ! ’

ጠርሙስ ውስጥ የቀረውን ቢራ አንሥቶ ጅው አደረገው ። ጉሮሮው ላይ እየተናነቀው ለምን በግድ እንደሚጠጣ መመራመር አልፈለገም ። ብኸ አለበት ቻቻታ ! ትርምስ ! ብኸኸ ኸኸ ! . . . ራስን የሚረሱበት ዓለም ።

ድፍረት ድፍረት አለው ። እልህ ተናነቀው ። ማንን እንደሚደፍር ፣ በማን ላይ እልሁን እንደሚወጣ ግን አያውቅም ።
“ ስማ እስክንድር ! ” አለው ፣ ሣቅ እየተናነቀው ወደ እስክንድር ፊት ተጠግቶ ፣ “ እኔ ትዕግሥትን እወዳታለሁ ። እሷ ግን አይገባትም ። እ — አይገባትም ። ”

እስክንድርና ሳምሶን ተደናገጡ ። ድንገተኛ አርዕስት ሆነባቸው ። አቤል ግን አርዕስቱን በልቡ ከጀመረው ቆይቷል ። ያም ሲሆን ጉዳዩን ሁለቱም አላጡትም

“ ከወደድካት] ይገባታል እንጂ ፣ አቤል ። ለምን አይገባትም ። ችግሩ ሁለታችሁም ተቀራርባችሁ ያለመነጋገራችሁ ነው ” አለ እስክንድር ፣ ፈራ ተባ በሚል ድምፅ ።

ከአሁን በፊት በግልጽ ተነጋግረውበት የማያውቁት ጉዳይ መነሣቱ፣ በእስክንድር ላይ ሁለት ስሜት አሳደረበት ።

በአንድ በኩል እውነቷን ከአቤል ለመስማት ሲጓጓ ስለ ከረመ ደስ ብሎታል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ አቤል ምስጢሬ ብሎ የያዘውን ነገር በስካሩ ጊዜ ማውጣጣቱ፣ ሲውል ሲያድር ትዝብት ላይ የሚጥለው መሰለው ። በመጨረሻ ግን ‘ ነገሩን እሱ ጀመረው እንጂ እኔ አልጀመርኩት ’ ብሎ ተጽናና ።

“ የምትወደኝ ከሆነ ለምን ዝም ትለኛለች ? እየሀ እስ ክንድር ፣ እኔ ’ ኮ ትዕግሥትን ሳላያት ውዬ ማደር አልች ልም ። ምርኮኛዋ ነኝ ። ምርኮኛዋ ስለሆንኩ እፈራታለሁ ። ላነጋግራት አልደፍርም ። እሷ ለምን ዝም ትለኛለች ? የራሱ ጉዳይ ብላ አይደለም ? ! ”

ሲናገር ዕንባውን ወደ ውስጥ ለመግታት እየታገለ ነበር ። እስክንድርና ሳምሶንም ልባቸው ዐዘነ ።

“ ትዕግሥትም ለአንተ የግዴለሽነት ስሜት ያላት አይ መስለኝም ” አለው እስክንድር ፣ “ ተገናኝታችሁ መነጋ ገር ስላልቻላችሁ ነው እንጂ ፣ እኔ እንደሚገባኝ እሷም ያንተኑ ያህል ትወድሃለች ። ”

“እሺ ይሁን ። እሷ ምናልባት ትወደኝ ይሆናል ። ነገር ግን በመሐላችን ምቀኞች አሉ ። ጓደኞቿ ናቸው የሚመ ክሯት ። በተለይ ያቺ ማርታ ! ”

“ እሷም ለአንተ መጥፎ ስሜት የላትም ። አቤል ሙት እልሃለሁ ። እኔ በቅርብ ዐውቃታለሁ ” አለው እስክንድር ።

“ ዋናው ችግር ምንድነው ? ለምን እኛ አንረዳውም ? ” አለ ሳምሶን ፣ ክልቡ ተቆርቁሮ ።

“ ለመርዳቱ በዘንን ብለህ ነው ፤ ችግሩ የቀላል ከባድ ሆንና ነው እንጂ ! ” አለው እስክንድር ቀስ ብሎ ።

“ ምን መሰላችሁ ፣ እኔ በእሷ ያልሆንኩት ነገር የለም ። እ — ብቻ — እኔ ብቻ ነኝ ስለ ራሴ የማውቀው ” እያለ ከተ ቀመጠበት ተነሣ ። ወንበሩን ሲለቅ ትንሽ ተንገዳገደ ።

“ ወዴት ትሔድ ? ” አለው እስክንድር ።
“ ወደ ሽንት ቤት ። በየት በኩል ነው ? ’

እስክንድር በምልክት አሳየው ። በዚያ ሁሉ ጠጪ መሐል ሁለት እጁን እኪሱ አድርጎ ፣ ሁሉንም በንቀት ዐይን እየተመለከተ ነበር - ወደ ሽንት ቤቱ የሔደው ።

“ ቢራዋ ሥራዋን እየሠራች ነው ” አለ እስክንድር ፣ የአቤልን አረማመድ እያየ ።

“ ግን ምን ይሻለዋል ? ” አለ ሳምሶን ፣ በአቤል ሁኔታ በማዘን ፣ “ አሁን በማዕረግ የሚመረቅ ይመስልሃል ? ”

እስክንድር ገርሞት ሣቀ ። የሳምሶን ጥያቄ ግን ከቅን መንፈስ የመነጨ ነበር ። አቤል የሚወደውም የሚያከብረ ውም በማዕረግ ተማሪነቱ ነው ። የአቤል የማዕረግ ተማሪነት በዩኒቨርስቲው ውስጥ በብዙ ተማሪዎች ዘንድ ይታወቃል ። እንደ እስክንድር ጠጋ ብለው የማያውቁት አሁንም የዓመቱ የፕሬዚዳንት የከፍተኛ ማዕረግ ሽልማት ከአቤል እጅ አይ ወጣም የሚል ግምት አላቸው ። ሳምሶንም የመኝታ ክፍል ጓደኛው ቢሆንም ቅሉ ፣ በትምህርት ያን ያህል መድከሙን አያውቅም ነበር ።

“ እውነቴን ’ኮ ነው ። ምን ያሥቅሃል ? ”

“ ማዕረጉ ቀርቶ በዚህ ዓመት መመረቁ ራሱ ነው እኔን የሚያጠራጥረኝ ” አለው እስክንድር ፣ በኀዘን ስሜት ፊቱ ተለዋውጦ ።

“ ያሳዝናል ! ግን ምን ታረገዋለህ! ” አለና ሳምሶን ፣ ቢራውን ከጠርሙሱ ውስጥ እየጨለጠ ፣ “ በነገራችን ላይ ፣ መውደቂያችንን እናዘጋጅ እንጂ ! መቼም ዛሬ ወደ ካምፓስ አንገባ ” አለው ።

እስክንድር የሳምሶን ሐሳብ ገባው ፤ አንድ ሴሚስተር ሙሉ ታፍኖ የቆየ ስሜቱ ተነሣሣ ። ነገር ግን ኪሱ እስተ ማማኝ አልነበረም ።

“ እኔጋ በቂ ገንዘብ የለማ ! ” አለው ልመና በተቀላቀ ለበት ድምፅ - ከልቡ ተዝናንቶ ።

“ አቤልም እሺ የሚል አይመስለኝም ። ከአሁን በፊት ውጭ አድሮ አያውቅም ። ”

" ምን ትቀልዳለህ ? ጭራሽ ? እምልህ . . . "

" አዎ ፡ ከእኔ ጋር ስንተዋወቅ ይኸው አራት ዓመት አለን ። አንድ ቀንም አድርጎት አያውቅም ። "

" እንግዲያው ዛሬ ድንግሉን ማስወሰድ አለብን ? " አለ ሳምሶን ፡ ተንኮልም የፍቅር ስሜትም እየተሰማው ።

" እዬዬ ! ተው እባክህ ! " አለ እስክንድር ፡ በተዘበራረቀ ስሜት ።

" ምናለበት ? አንተ ደሞ ! እንዲያውም ሴት ከቀመሰ የዐይኑ ፍቅር ይለቀው ይሆናል ። ገንዘብ እንደሆን እኔ ይገኘለሁ ብዬሃለሁ ። "

እስክንድር የሳምሶን ሁኔታ ራሱ እንግዳ ሆነበት ። ሳምሶን አብዛኛውን ጊዜ በኪሱ በርካታ ገንዘብ ይይዛል ። ወላጆቹ ደኅና ገቢ አላቸው ። አባቱ በአንድ ኢንተርናሽናል ድርጅት ውስጥ በጥሩ ደመወዝ ይሠራሉ ። በእናቱ ስም ደግሞ መስጊድ አካባቢ የሰዓት መሸጫ ሱቅ አላቸው ። ወላጆቹ ለሳምሶን በወር ተቆራጭ ካደረጉለት ሃምሳ ብር ሌላ ፡ ሊጠይቃቸው ብቅ ባለ ቁጥር አንድ ወይም ሁለት ባለ አሥር ኖት ሳያሸጉት አይመልሰም ። ታዲያ ሳምሶን ይህን ሁሉ ገንዘብ ሲይዝ ፡ ለመጠጥ ማጥፋት አይወድም። የሱ ገንዘብ የሚያልቀው በምግብ ነው ። መብላት ፡ ስፖርት መሥራት - ግን ባታ ብቻ ! በዩኒቨርስቲው አቅራቢያ ካሉት ምግብ ቤት ባለቤቶች ውስጥ እሱን የማያውቅ የለም ። ዛሬ ገንዘቡን ለመጠጥና ለሴት ለማውጣት መዘጋጀቱ ነው - እስክንድርን ያስገረመው ።

" እንዴት ነው ? ዛሬ ግንባታው ቀርቶ ለማፍረስ ነው መሰል የታጠቅከው " አለው እስክንድር እየሣቀ ።

"እንዳንዴ ያስፈልጋል እባክህ ! "

አሳላፊዋ አራት ጠርሙስ ቢራ ይዛ መጣች ። አንዷ ለራስዋ መሆኑ ነው ።

" ቢራ እዚሁ ጓዳ መጥመቅ ጀመራችሁ እንዴ ? " አላት እስክንድር ፡ ከታዘዘች መዘግየቷን ለመጠቆም ።

" ቆየሁ እንዴ ? አንድ ሰካራም ይዞ ሲነተርከኝ ኮ ነው " አለች ፡ ቢራውን እየከፈተች ።

" አንቺው መጠጥ አቅርበሽለት አንቺው፡ሰካራም ትይዋለሽ ? በይ ነይ በይ " አለና ሳምሶን ፡ ዳሌዋ ላይ ቸብ አደረጋት ። ቸብታው ጠንከር ያለ ስለ ነበር ዳሌዋን ለበለባት ።

" እንደዬ ! ታዲያ ዱላው ምንድነው ? " አለች ፡ ተቆጥታ ዳሌዋን በእጅዋ እያሻሸች ።

" ዝም በይና ቁጭ በይ ! ከፈለግኩ ጥርስሽን ነው የማረግፈው " አላት ሳምሶን ፡ እንደ ልማዱ ።

እስክንድር ነገሩ ማየሉን ሲያይ ተደናገጠ ።

" ኧረ እባክህ ! የማነህ ሒድና የሚስትህን ጥርስ አውልቅ ። የእኔን የብርቅነሽን አይደለም ። ስለ ቢራው እንደሆን ኬረዳሽ ! " ብላው የከፈተችውን ቢራ ጥላ ተነሣች ።

ብርቅነሽ አምርራ ልትሔድ ስትል፡እስክንድር እጅዋን ይዞ አባብሎ አስቀመጣት ።

" አንቺ ደሞ እረፊ እንግዲህ ። እሱ ለጨዋታ ያህል ነው የነካሽ "

እየተመናቀረች ከሳምሶን ርቃ እስክንድር ጎን ተቀመጠች ። ሳምሶንም ጥርሱን እያንቀጫቀጨባት ነበር ። በማይረባ ነገር ተለካክፈው የጎሪጥ መተያየታቸው እስክንድርን አስገረመው ።

" ሁለታችሁም ዕረፉ ፡ ይሄ ቡና ቤት ነው ። በሰላም ጠጥተን መጫወት ነው የምንፈልገው " አላቸው ፡ ከግንባሩ ኮስተር ብሎ ፡ ግን በሆዱ እየሣቀ ።

የእስክንድር ሐሳብ እነሱጋ ረግቶ አልቆየም ። በድንገት አንድ ሐሳብ አእምሮውን ወጋው ። አቤል ወደ ሽንት ቤት ከሔደ ቆይቷል ፤ ግን አልተመለሰም ። እስክንድር ልቡ መጥፎ ነገር ጠረጠረና ድንገት ከተቀመጠበት ተነሣ ።

" ምነው ? " አለው ሳምሶንም ፥ በሁኔታው ተደናግጦ ።

" ምንም አይደለም ፥ መጣሁ " ብሎ እስክንድር ወደ ሽንት ቤቱ ሔደ ። አቅለሽልሾት ይሆናል በሚል ግምት ሳምሶን ነገሩን ቸል አለው ።

እስክንድር ከመጸዳጃ ቤቱ አጠገብ ሲደርስ፥አቤል እጁን በኪሱ እንዳደረገ ግድግዳ ተደግፎ ቆሞ ነፋስ ሲቀበል አገኘው ። ዐይኑ በርበሬ መስሏል ። ፀላፊ አግዳሚውን በንቀት ዐይን ነው የሚመለከተው ።

" ቴክሱ ! ምነው ? " አለው እስክንድር ፥ ደኅና መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ።

" ወረፋ ሆኖብኝ ነው እባክህ ! "

" የሽንት ቤት ወረፋ ? በል እንግዲህ ጠብቅ ። ምን ታረገዋለህ ? " ብሎት እስክንድር ወደ መጣበት ተመለሰ ። አቤል አንድ አደጋ ደርሶበታል የሚል ሥጋት ስለ ነበር፥በሰላም በማግኘቱ ልቡ ተረጋጋ ። ምንጊዜም አያምነውም ። አንድ ቀን በራሱ ላይ የሞት ቅጣት ይፈርዳል የሚል ፍራቻ አለው ።

ወደ መቀመጫው ሲመለስ፥ብርቅነሽና ሳምሶን ተስማምተው ጎን ለጎን ተቀምጠው ሲያወሩ አገኛቸው ።

" ታረቃችሁ እንዴ ? "

" ዱሮስ መች ተጣላን ? አንተ ደሞ " አለችና ብርቅነሽ ጠየቀችው ።

' ቀድሞውንም ጸበኞች የሚገባበዙት መሐላቸው ገላጋይ ሲኖር ነው ። ብቻቸውን ሲሆኑ እንደኛው ዐቅሙን ዐውቆ ወይም ጥቅሙን ከጉዳቱ አመዛዝኖ ጸባዩን ያሳምራል ' አለ እስክንድር በልቡ ።

" ያንን ነገር 'ኮ ለብርቅነሽ ነገርኳት " አለው ሳምሶን ፥ ዐይኑን እስክንድር ላይ ተክሎ ።

" የቷን ነገር ? "

" የአቤልን ነዋ ! በቃ ፥ እሷ ይዛው ትደር ። "

ሳምሶን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መሆናቸውን አጫውቷት ፥ ከዚያው ቡና ቤት መኝታ እንድትይዝ ገንዘብም ሰጥቷታል ።

" አንተ ዛሬ የልጁን ድንግል ለማስወሰድ ታጥቀህ ተነሥተሃል ማለት ነው ? " አለ እስክንድር ፥ ንግግሩ አስገርሞት እየሣቀ ።

" መሆን አለበት ብዬሃለሁ ። አድቬንቸር ነው ። "

" እንቺስ ? በነገሩ ተስማማሽ ? " አላት እስክንድር ፥ ፊቱን ወደ ብርቅነሽ መልሶ ።

" ውይ ፥ በደስታ ነዋ ! እንዲያውም ድንግል ወንድ ደርሶኝ አያውቅም ። ዕድሌ ሆኖ የተፈተኑ ብቻ ነው የሚደርሱኝ ። "

ስትናገር ሣቅ ሣቅ ስለምትል የቀልዷን ይመስላል እንጂ፥ ብርቅነሽ የምትናገረው የልቧን ነበር ። ወሲብ ጀማሪ ገጥሟት አያውቅም ። ለልጅነት ባሏም ቢሆን ሁለተኛ ሚስቱ ነበረች ። ቡና ቤቱ ውስጥ የሥራ ጓደኞቿ ፥ " ዛሬ የአንዱን ጀማሪ ድንግል ወሰድን " እያሉ ሲያወሩ ትቀናለች ። በዚህ ወሬ የቀካነችው የቡና ቤቱ ባለቤት ነች ። የጥንት ዝናዋን ስታወራ ይሄ አርዕስት ከመሐል አይጠፋም ። የቀትር ቡናዋን እያፈላች በሸርሙጦች ተከባ ውቃቢዋን ስትለማመን ንግግር መክፈቻዋ ይኸው ነው ።

" አይ ዘመን ! ስንቱ ዐለፈ ? ! ቡና ቤቱ እንዲህ እንዳሁኑ ሳይደራጅ ሠራተኛ ሠፈር ትንሽ ኪዮስክ ከፍቼ ነበር የጀመርኩት ። ታዲያ ያኔ ስንቱን ባላገር ገራሁት መሰላችሁ ! መቼም የሰው ነጭ ነው ያየሁበት ። ፍቅር በድሪያ የሚይዝ ቢሆን ቀልጬ እቀር ነበር ። አበስኩ ! ዕረፍት ሳላገኝ ነበር የምውለው ። ታዲያ በጣም ትዝ የሚሉኝ ገና ልጅነታቸውን ያልጨረሱ ተማሪዎች ናቸው ። በምሽት ተሰርቀው

ብቅ ይሉና ድንግላቸውን አስረክበው ይመለሳሉ ። ምን የመሰሉ ሎጋዎች ነበሩ ! ”

አንዴ ከጀመረች ማቆሚያ የላትም ። ዐይና ዕንባ እስኪያቀር ድረስ የጥንት ኑሮዋ ውስጥ ሰምጣ ትቀራለች ። በዚህ ጊዜ ብርቅነሽ በልቧ ትቀናለች ።

“ ምነው ፈዘዝሽ ? ” አላት እስክንድር ፣ በሐሳብ ጭልጥ ብላ መሔዷን እያየ ።

“ መፍዘዝ ሆሆይ ! እንኳን ፈዘን ቀልጥፈንም አልሆን ልን ” ስትል አቤል ተመልሶ መጥቶ አጠገባቸው ተቀመጠ ።

“ ኖር ብለናል ” አለችው ፣ ሞቅ ካለ ፈገግታ ጋር ።

ስትሥቅ ድዷ ይታያል ። የላይኛው ድዷን ጉራማይሌ ተንቅሳዋለች ። አንገቷ ንቅሳት ፣ ድዷ ንቅሳት አቤል ያሜሩ በትን አላወቀም ። የተከፈተለትን ሦስተኛ ቢራ ልጠጣው ወይስ አልጠጣው በሚል ስሜት ዝም ብሎ ተመለከተው ።

“ ይሄ ነገር ቢበቃኝስ ? ” ሲላቸው ፣ ምላሱ ትንሽ ትንሽ መተሳሰር ጀምሯል ።

“ ኧረ ጠጣ ! ምን እንዳይልህ ? ዕረፍታችሁ አይደለም እንዴ ? ” አለችው ብርቅነሽ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ዐይን ለዐይን ተያዩ ።

“ ስሚ ብርቅነሽ ፣ ይህ ሁሉ ንቅሳት ምንድነው ? ” አላት እስክንድር ፣ ጣልቃ ገብቶ ። ለለከፋ መሆኑ ገብቷታል ።

“ ጌጥ ነዋ ! ምን አገባህ አንተ ደሞ ? ”

“ ማለቴ ፣ አዲስ አበባ ስትገቢ ልታጠፊው አልሞከርሽም ? ”

“ ውይ ፣ ለምን ብዬ ! ቁምጥና መሰለህ ? ”

“ እሱን ተይው ! የሚቻል ቢሆን ኖሮ ሴቶች ንቅሳታችሁን ለማጥፋት የማትገቡበት ጉድጓድ አልነበረም ። ለመሆኑ ከሀገርሽ ከወጣሽ ስንት ጊዜ ሆነሽ ? ”

“ ምናገባህ ? ሞዛዛ ! ” ስትለው ድምጿ የብሸቀት ቅላጼ ነበረው ።

“ እውነት ብርቄ ፣ ምን ያህል ጊዜ ሆነሽ ? ” አላት ሳምሶንም ተደርቦ ።

“ አራት ዓመት ! ”

“ የአራት ዓመት የሥራ ልምድ ! ከሌሎች አንጻር ሲታይ ትንሽ ነው ” አላት ሳምሶን ።

“ መላጣ ! ” አለችው ፣ ጭንቅላቱን በዐይኗ ቂጥ እያየች ።

“ በአራት ዓመት ውስጥ ስምሽን ለመለወጥ አልሞከርሽም ? ” አላት እስክንድር ሲቀልድባት ፣ “ አዲስ የከተማ ስም እንደ ራሄል ፣ ኤደን ፣ ማርታ ፣ ዓለም — ከተሜ ለመሆን ፣ እ ? ”

“ ሒድ ፣ ደረቅ ! ”

ሒድ ፣ ደረቅ ! ሒድ ፣ ደረቅ ! ደረቅ ! ማርታ በቅናት ቅንድቧን እያርገበገበች ከፊቱ ድቅን አለችበት ። በሐሳቡ ቁመናዋን ቃኘ ። በሞቅታ መንፈስ እንደገና አለማት ። ኪሱ ባዶ ። ማለም ብቻ ! ማነጣጠር ብቻ !

‘ ሒድ ፣ ደረቅ ! የሴቶች የጋራ ፈሊጥ ’ አለ በልቡ ።

የብርቅነሽ ጥሬነት አስገረመው ። ስትጫወት የባላገር ለዛ አላት ። ንቅሳቷ ባላገርነቷን ይመሰክራል ። የባላገር ስሟን አልለወጠችም ። እምብዛም የከተሜ ጭምብል አላጠለቀችም ።

“ ግን ከሀገርሽ ለምን ወጣሽ ? ” አላት በድንገት ።

“ ሆሆይ ! ጋዜጠኛ ነህ እንዴ ? ”

“ ባልሆን ፣ ይህን ሥራ ምን አስመረጠሽ ፣ ማለቴ ነው ። ”

"ዋ ! ወድጄን መሰለህ ? ግድ ሆኖብኝ እንጂ" ከማለቷ ፣ ፊቷ የኀዘን ጭጋግ ለበሰ ።

"ምነው ? እንዴ ?" አላት እስክንድር ፣ ስሜቷን ተከትሎ ስሜቱ እየዳመነ ።

"ባልተቤቴ ነው ለዚህ ያበቃኝ ! በሱ ምክንያት ነው ሀገሬን ለቅቄ የወጣሁት" እያለች የታሪኳን ዳር — ዳር ጨረፈችው ። በፍቅር ለቀረባት ሁሉ ታሪኳን ታወራለች ። ሊስልስ ሆኖ ለቀረባት የአንጀቷን ትዘከዝካለች ። የተማረ መስሎ ለታያት ችግሯን አፍረጥርጣ ትናገራለች ። መፍትሔ ይገኝልኛል ብላም አይደለም ። የውስጧን ተንፍሳ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የመንፈስ ዕረፍት ታገኛለች ።

"አባክሽ አታጓጊን ! በደንብ አጫውቺኝ" አላት እስክንድር ፣ ታሪኳን ለመስማት ተጣድፎ ።

"እያችሁ ፣ እናንተ ዕድለኞች ናችሁ ። ከደኅና ቤተሰብ በመወለዳችሁ ወይም ከተማ በማደጋችሁ ፣ ለመማር በቅታችኋል ። እኔ የቀለም ትምህርት የለኝም ። ማንበብና መጻፍ እንኳ የቻልኩት አሁን የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ከተጀመረ ወዲህ ነው ። የደሀ ገበሬ ልጅ ነኝ ። ያውም በእንጀራ እናት ያደግኩ ! ህም ! እቴ ! ታዲያ ገና በዐሥራ አራት ዓመቴ ተዳርኩ ። ባሌ ገበሬ ነበር ። እኔ ሁለተኛ ሚስቱ ነኝ ። የመጀመሪያ ሚስቱ ከተጋቡ መንፈቅ እንኳ ሳይሞላቸው ሞታበት ነበር ። ወላጆቼም ሲድሩኝ ይህን ያውቃሉ ። 'በዕድሜ በሰል ያለ ነው ። ጸባዩም ጥሩ ነው ። ለትዳሩ ታታሪ ነው' ተባለና ተሰጠሁ ።

"ጎጆአችንን እያሞቅን ፣ የባላባቶቹን ግልምጫና ዱላ በጋራ እየተቀበልን መኖር ጀመርን ። ምን ይሆናል ። እግዜር ለተንኮሉ ማሕፀኔን ድፍን አደረገው ። ዓመት ጠበቅን ፣ ሁለት ዓመት ጠበቅን ፣ ልጅ የለም ። በእኔና በባልተቤቴ መሐል ቅሬታ መጣ ። ያም ሆኖ አልተቃቃርንም ። ድህነት ያስተሳሰረን ነበር ። እሱ ከገበሬዎቹ ጋር ውጭ ደክሞ ውሎ ሲመጣ ከቤት ያለሁ ፣ ረዳቱ እኔው ነበርኩ ። በባላባት ጅራፍ ጀርባው ቆስሎ ሲመጣ ፣ አንጀቴ እየተንሰፈሰፈ የማለቅስለት እኔ ነበርኩ ። ዋ እቴ ! ምን ያረጋል !

"እንዲህ እንዲህ እያልን አምስት ዓመት ያህል እንደኖርን አብዮቱ ፈነዳ ። ለውጥ መጣ ። ደክመን ለባላባቱ መገበር ቀረ ። እፎይ አልን ። ቤታችን ሙሉ ሆነ ። እውነቴን ነው ። ደኅና ነገር መብላትም መልበስም ጀመርን ። ምን ይሆናል ፣ ከደኅና ኑሮ ጋር ተያይዞ ነገር መጣ ። ባልተቤቴ ሌላ ሴት በስርቆት መሔድ ጀምሯል የሚል ወሬ ሰማሁ ። ሰውል ሳድር እኔም ነገሩን ደረስኩበት ። እንዲያውም አንድ ልጅ እንደወለደችለት አረጋገጥኩ ። ቀናሁ ! ቅናት አንገበገበኝ ። በሐሳብ ተብከነከንኩ ። ጨስኩ ። ቤት ውስጥ መቀመጥ አቃተኝ ። ብዙም ሳልቆይ ፣ ጓዝ ምንንዝ ሳልል በርሬ ወጥቼ አዲስ አበባ ገባኋት !

"እዚህ ስደርስ ደግሞ ያዘጋጀሁት ማረፊያ የለኝ ፣ እንደው ሜዳ ቀረሁ ። ትንሽ ቀን ስንብቼ በደላላ አማካይነት ግርድና ተቀጠርኩ ። ስድስት ወር እንደ ሠራሁ ግርድናን እርም ብዬ ተውኩት ። አበስኩ እቴ ! የሰው ቤት ! ሹሮ ሲያልቅ እኔ ላይ ማፍጠጥ ። ዕቃ ሲጠፋ እኔን መወንጀል ። ምነው ከዚህ ሁሉ ሥጋዬን ሽጬ ባድር አልኩና ሽርሙጥና ጀመርኩ እላችኋለሁ ።"

ብርቅነሽ ስትናገር ታላቅ ማዕበል ተነሥቶ ባሕር ውስጥ የከተታቸውን ያህል ሦስቱም ጸጥ ብለው ነበር ። አሳዘነቻቸው ። ምስኪን ጥሬ ፍጥረት ! በመጠጥ ሞቅታ ኃይል ለሁሉ ነገር ግዴለሽ ሆኖ የቆየው አቤል እንኳ ፣ ከብርቅነሽ አፍ የድህነት ድምፅ ሲሰማ ቸል ማለት አልቻለም ። ሕዋሳቱ በኀዘን ስሜት ተወራጨ ።

"ግን ዝም ብለሽ ከምትኮበልይ ፣ ለምን በአካባቢሽ ለሚገኘው የሴቶች ወይም የገበሬ ማኅበር አመልክተሽ መፍትሔ አትፈልጊም ነበር ?" አላት እስክንድር ፣ ከማዘኑ የተነሣ የሚናገረው ጠፍቶት ።

"ዋ እቴ ! ቤት ከፈረሰ ወዲያ ሁሉስ ምን ሊበጅ ? አየህ ፣ ቅናት ከመጣ ቤት ፈረሰ ማለት ነው ። ለሁሉም እኔ ለማንም አላማከርኩ ። የሚያለቅሱ ልጆች የሉኝ ፣ ነጣላ ሰው ምናለበት አልኩና ብር ብዬ አዲስ አበባ !"

" ታዲያ ባልሽ ሊፈልግሽ አልመጣም ? " አላት አቤል ፣ በሁኔታዋ ስሜቱ ተነክቶ ።

" ውእእይ ፣ ሥራ አጥቶ ! እንዲያውም ከዚያ ሀገር ለን ግድ የሚመላለሱ ሰዎች እዚሁ ቡና ቤት አግኝቼ ሲነግሩኝ ፣ ውሽማውን ጠቅልሎ ይዟል አሉኝ ። እዬዬ ! " ብላ ሳት ጨርስ ጥሬ ሰማች ።

" ብርቅነሽ ? ! እንቺን'ኮ ነው ? " — የቡና ቤት ባለ ቤቷ ድምፅ ነበር ።

" እመት ! ወይ ጉዴ ዛሬ ! " እያለች ብርቅነሽ ከተቀ መጠችበት ተነሣች ።

" እንድዬ ! ሰው ሲገባ አትታዘዥም እንዴ ? ምን ይጎ ልትሻል ? "

ብርቅነሽ የውስጧን ተንፍሳ ቃጠሎዋን አብርዳ ተነ ሣች ። እስክንድር ተከዘ ። ቃጠሎዋ ወደ እሱ ተላለፈበት ። ኀዘኗ ጠልቆ ወጋው ። ቅናት ተፈጥሮአዊ ነው ። ሀብታምና ድሀ አይልም ። የወደደ ሁሌ ለወደደው ነገር ይቀናል ። ለቀ ናበት ነገር ይሠዋል ። ብርቅነሽ የቅናትን እሳት ሽሽታ ኮበ ለለች ። ከቅናት ሽሽታ ሴትኛ አዳሪ ሆነች ።

እስክንድር ሐሳቡ ከግላዊነት ወደኅማኅበራዊነት መጠቀ ። ለእሱ ሲጋራ መግዣ መስጠት ያቃታቸው ደሀ እናቱ ሳይ ሆኑ ፣ ሕዝቧን በሰፊው ማስተማር ፣ በቂ ኢንዱስትሪ ከፍታ እነብርቅነሽን ማሠማራት ያልቻለች ፣ ረሀብን ለማጥፋት ፣ ማይምነትን ለማጥፋት ፣ ርካሽ ልምዶችን ለማስወገድ ፣ በባ ህል ለማደግና የቴክኖሎጂ ውጤት ተጠቃሚ ለመሆን የል ጆቿን እጅ የምትማጠን እናት ሀገር ፣ እጆቿን ዘርግታ በሐ ሳቡ ታየችው . . .

ከሐሳቡ ፋታ አግኝቶ እሱነቱን ወዳለበት ሲመልስ ሳምሶን ዐይኑን አፍጥጦ ተመለከተ ። አስተያየቱ አላማረ ውም ። በልቡ ፣ " ምርምርህን እዚያው ዩኒቨርስቲው ውስጥ አድርገው ፣ ይሄ መጠጥ ቤት ነው " የሚለው መሰለው ።

እና እስክንድር ብርጭቆውን አነሣ ። መጠጣት ! ለጊዜውም ቢሆን ራስንም አካባቢንም ለመርሳት ፣ ኀሊናን ለማዘናጋት መጠጣት !

" ስማ እንጂ እስክንድር ፣ እየመሸ 'ኮ ነው ! " አለው ሳምሶን ዐይኑን አጉረጥርጦ ።

" እ ? እሺ ፣ እንሒድ እንዴ ? "

ሁለቱም የብርጭቆአቸውን አጋብተው ብርቅነሽ እስ ክትመለስ ጠበቁ ። አቤል ሦስተኛው ቢራ ላይ ፀግማሽ ተሸ ንፎአል ።

የብርቅነሽም ልብ ከእነሱው ጨዋታ ጋር ቀርቶ ስለ ነበር ፣ የታዘዘችውን በፍጥነት አቀራርባ ተመለሰች ።

" መሔዳችን ነው እንግዲህ " አላት እስክንድር ፣ ለመ ነሣት እየተንጠራራ ።

" ተጫወቱ እንጂ ፣ ምነው ? " አለች ፣ አቤል አጠገብ እየተቀመጠች ።

" እንሒድ እባክሽ ! ገና መውደቂያችንንም አላዘጋ ጋጀን " አላትና ፣ " አንቺም ከሦስታችን አንዳችንን ይዘሽ ማደር አለብሽ " አላት ።

" ከሦስታችሁ በዕድሜ ልጅ የሆነውን ነው የምፈ ልገው ። "

" እንዴት ታውቂያለሽ ? ግንባራችን ላይ አልተጻፈ ! "

" ውይ በደንብ ያስታውቃል ። አሁን ለምሳሌ እሱ በዕድሜ ልጅ ነው " አለች አቤልን እንደ ማቀፍ ክንዷን ትከሻው ላይ ጣል አድርጋ ። " ሳምሶንም ሰውነቱ ፋፋ እንጂ ጢም እንኳ የለውም ። ባንዴ የተመዘዘ ሰውነት መሆኑ ያስታውቃል ። "

" እናትሽን ! " አላት ሳምሶን ፣ ሣቅ አፍኖት ።

" በይ ቀጥዪ ። እኔስ ? " አላት እስክንድር ።

" አንተ እንኳ ጠንዝተሃል ፣ ታስታውቃለህ " አለ ችው እየሣቀች ።

" ያጠንዛሽ ! " አለ እስክንድር ፣ በልቡ እየሣቀ ወደ አቤል ጆሮ ተጠግቶ ፣

" ከእንግዲህ የካምፓስ ፖሊሶች አያስገቡንም ። መሽቷል ። እዚሁ ከብርቅነሽ ጋር ማደርህ ነው " አለው ።

አቤል በቋንቋ መልስ መስጠት አልቻለም ። በእሺታ ቅንድቡን ሽቅብ ቀልሶ ፈቃደኛነቱን ገለጸ ። ፍላጎቱ አለው ። ግን እንዴት ይሆናል ? ያለ ገንዘብ ይታደራል እንዴ ?

" አይዞህ ፣ ችግር የለም " አለው ሳምሶን ፣ ግር እንዳ ለው አይቶ ።

አቤል በአልኮል የደከሙ ዐይኖቹን እንደገና አስለም ልሞ በእሺታ ግንባሩን ነቀነቀ ።

የአቤል የደከመ ገጽታ በእስክንድር ላይ አንዳች የኀ ዘን ስሜት ፈጠረበት ። ለእምነቱ ግትር የነበረው አቤል ከፉኛ እየተረታ መምጣቱን ገመተ ። እነሆ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሴት ጋር ውጭ ለማደር ፈቃደኛ ሆነ ። ሴት ልጅ ክንዷን ትከሻው ላይ ስታደርግ ወይም ስታቅፈው ተቃውሞ አላሳ የም ። በዚች ቡና ቤት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ትዕግ ሥት ከአፉ አውጥቶ ተናገረ ። በእምነት ግትርነት ተወ ጣጥሮ የቆየ እሱነቱ ላላ ። ይህ መጠጡ የፈጠረው የአካል ድካም ብቻ አይደለም ፤ የመንፈስ መድከም ነው ። መንፈስ ሲደክም ደግሞ አካልም ይዝላል ። ምላስም ይተሳሰራል ። ሰውነት ከአድራጊነት ወደ ተመልካችነት ወይም ታዛቢነት ይሸጋገራል ።

እስክንድር በልቡ ይህን እያሰበ ፣ ' ታዲያ አቤል ጓደ ኛዬ መንፈሱ ሲደክም ፣ በማበረታታትና የቀድሞ እምነቱን በመጠበቅ ፈንታ ፣ ሲሸሸው ወደ ቆየው ተግባር መጨመሩ ትክክል ነው ? ' ሲል ራሱን ጠየቀ ።

' ያስፈልጋል ! አንዳንዴ ራስን መርሳት ያስፈልጋል ። ሁልጊዜ ራስን እስታውሶ እንደ ምን ይቻላል? አቤልም ዛሬ ራሱን ይርሳ ! እርሱነቱን በተለየ ገጽታው ይመልከተው ። ሕይወት ዥጉርጉር ናት ' እያለ ሲያስብ ፣ አልኮል የማይ በግረው ጎሊናው ጠሩን መዝዞ ተነሣበት ። እስክንድርም ጋሻ ይሆነው ዘንድ የቢራ ጠርሙሱን አነሣ ። ነገር ግን ጠርሙሱ ባዶ ነበር ።

" እንሒድ እንጂ ፣ መኝታ ከያዝን በኋላ ከፈለግክ ሌላ ጋ እንጠጣለን " አለው ሳምሶን ፣ በቁጣ ድምፅ ።

ወዲያውም ሒሳቡን ከፍሎ ተነሣና ብርቅነሽን ጠቀ ሳት ። እስከ ውጭው በር ተከተለችው ። ገንዘብ በእጅዋ ሲያስጨብጣት " ዋ ! ልጁ ምንም አያውቅም ብለሽ እንዳትፈነግይው ! " ሲል አስጠነቀቃት ።

" እኔ ብርቅነሽ ? ሥራዬም አይደል ። ይልቅ ቻው ! " ብላው ገባች ።

እስክንድር ከአቤል ጋር ጠዋት ጆሊ ባር ለመገናኘት ቀጠሮ ሰጥቶት ወጣ ።

" ሳምሶን ፣ ብቻ ዛሬ በረንዳ እንዳናድር " አለው እስክንድር በሥጋት ።

" ግድ የለህም ፣ ገና ሰዓት አለን " አለ ሳምሶን ፣ ፊት ፊት እየቀደመ ።

ሁለቱ ከሔዱ በኋላ ፣ አቤልና ብርቅነሽ ተፋጠው ቁጭ ሆኑ ። ከመሐከላቸው ቃል የሚተነፍስ ጠፋ ። ብርቅነሽ ዐልር ዐልፎ " ተጫወት እንጂ " እያለች ብትጎተጉተ ውም ፣ አቤል ምላሱ ሊፍታታለት አልቻለም ። ወንድ ፣ ሴት ልጅን ምን እያለ ማጫወት እንዳለበት ገና አላወቀም ።

" ወይም መኝታ ከፍልህን ላሳይህ ? ዐረፍ የምትል ከሆነ " አለችው ።

" ብቻዬን ? " አላት ፣ ድምፁ በመጠጡም በፍር ሀቱም ተወሲጋግዶ ።

“አእይ እኔም እመጣለሁ ። ነገር ግን ከአምስት ሰዓት ተኩል በፊት ሥራ ለማቆም ባለቤትየዋ አትፈቅድልኝም ። እስከዚያ ድረስ አንተ ገብተህ ዐረፍ በል ” አለችው እየማቀች ።

“እሺ ፀይ አሳዪኝ ። ”

ከቡና ቤቱ በስተጀርባ ከሚገኝ አንድ ክፍል ውስጥ አስገብታው ተመለሰች ።

አቤል ቶሎ ልብሱን አላወለቀም ። አልጋው ላይ ተቀምጦ ጣራ ግድግዳውን ይመለከት ጀመር ። አልጋው ገና ቁጭ ሲልበት እሮሮውን አሰማ ። እየተንቃቃ አቃሰተ ። ለዕረፍት ሳይሆን ለድሪያ የተዘጋጀ አልጋ ። ክፍሉ የቤት መልክ አልነበረውም ። ሆኖም አቤል ይህን ሁሉ ለማጤን አልቻለም ። እግሩን ሳያወጣ በጎኑ አልጋው ላይ ጋደም ሲል ሰማይ ምድሩ ብዥዥ አለበት ። የሚሽከረከር መሰለው ። ዐይኑን ዘጋ ። አሁን ደግሞ ክፍሉ ሳይሆን የገዛ ጭንቅላቱ የሚሽከረከር መሰለው ። ብርቅነሽ በሐሳቡ መጥታ ዕርቃኗን ከፊቱ ቆማ ብዥታውን አበረደችለት ። ሰውነቱ በወሲብ ግለት ተወጣጠረ ። ቸኮለ ። ዐይኑን ሲገልጥ ግን ከፊቱ የቆመ ነገር አልነበረም ። ወና ቤት ! ወናነቱ ያስፈራል ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ጥንድ የመሆን ተስፋ በልቡ ባይቀረጽ ኖሮ አቤል ወናውን ክፍል ሸሽቶ በፈረጠጠ ነበር ።

ወናነቱን ላለማየት ወይም ቀድሞ ያየውን ዕርቃን ደግሞ ለማየት እንደገና ዐይኑን ጨፈነ ። የብርቅነሽ ዕርቃን በድጋሚ ሊታየው አልቻለም ። በምትኩ የሌላ ድምፅ በጆሮው ውስጥ አስተጋባ ።

“ ብር አምባር ሰበረልዎ !
ብር አምባር ሰበረልዎ !
ሸጋው ልጅዎ ! ”

የእስክንድር እና የሳምሶን ድምፅ መሰለው ። ጆሮው የሰማ የመሰለውን በዐይኑ ለማረጋገጥ ዐይኑን ገለጠ ። አሁንም ምንም ነገር የለም ። ዐይኑን እየጨፈነና እየገለጠ ከቅዠቱ ጋር በመጫወት ላይ እንዳለ እንቅልፍ አሸለበው ።

የክፍሉ በር ሲበረገድ ከእንቅልፉ ባነነ ። ብርቅነሽ ነበረች ። የደም ሰንበር በተጋደመባቸው ዐይኖቹ ውስጥ ግዙፍ ሆና ታየችው ። ንቅሳቷ ባለበት የሚርገበገብ መሰለው።

“ አልተኛህም እንዴ ? ”
“ እ ? ”
“ አልተኛህም ወይ ? ”

ገና ከመግባቷ ተወርውራ አጠገቡ ቁጭ አለች ። ዘለለና አቀፋት ። ቶሎ ልብሱን አወለቀ ። ጭኑና ጭኗ ስለ ተጠጋጋ ከፉኛ ሞቀው ።

“ እንዴ ቀና በል ፤ የኔ ሸጋ ። ”

“ እ ? ”

“ እንዴ ቀና በልልኝና በሩን ቆልፈ ልብሳችንን እና ውልቅ ። ”

ቁኖ ቁና እየተነፈሰ ቀና አለ ። የሴት ልጅ ገላ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጠጋቱ፣ በወሲብ ስሜት የልቡ ትርታ ከፉኛ ይነጥርበት ጀመር ።

ምዕራፍ ሀያዐንድ

ፀማግሥቱ ጠዋት ከቀጠሮው ሰዓት ቀድሞ ጆሊ ባር የተገኘው እስክንድር ነበር ። ያደረበት ቤት ስላልተስማማው በሌሊት ነበር ተሾልኮ የወጣው ። የቤቱ አለ መስማማት ብቻ ሳይሆን ፣ የሰው ዐይን ፍራቻም ነው “ አላሁ አክብር ” ሳይል ያስወጣው ። የገዛ ኅሊናው ዐይን ሲያለቅስ እንባውን አድርቆ ሲልከሰከስ እያደረ ፣ የሌሎችን ዐይን ለምን እንደ ሚፈራ ሁሌም ይገርመዋል ። ባደረበት ቤት አንግቶ ፣ ተዝናንቶ ቆይቶ አያውቅም ።

‘ ይህን ልምድ ከየት ይሆን የቀዳነው ? ’ ሲል አሰበ ። በዩኒቨርስቲው ውስጥ በትምህርት ወራት ቀለም ላይ ተደፍቶ መክረም ፣ በዕረፍት ሳምንታት ደግሞ ኪስ እስከ ተቻለ ድረስ በአልኮል ማበድና በየበረንዳው ማደር ፊሊጥ እየሆነ መምጣቱ ነበር ያሳሰበው ። በዛሬው ዕለት እንኳ እንደ እሱው የሰው ዐይን እየፈሩ ፣ ከያደሩበት በረንዳ በሌሊት እየተሾለኩ ፣ ጸጉራቸው እንደ ተንጨፈረረ ወደ ካምፓስ ሲሮጡ ያያቸው ተማሪዎች ቁጥር ትንሽ አልነበረም ።

‘ ሁኔታው በትምህርት ተጨንቆ የከረመን አዕምሮ የማዝናናት አዝማሚያ ይመስላል ’ ሲል ሐሳቡን ቀጠለ ። ‘ ታዲያ ከሰው ዐይንም ፣ ከገዛ ኅሊናም የማይሸሹበት ሌላ መዝናኛ መፍጠር አይቻልም ወይ ? ተማሪው ከተባበረ ፣ ከፌተና በኋላ ባለው የዕረፍት ጊዜ ውስጥ እንደየዓቅሙ ገንዘብ አዋጥቶ ፣ የሙዚቃና ሌሎች የተለያዩ ትርኢቶችን ፣ እንዲሁም አዝናኝና አነቃቂ ውድድሮችን ማዘጋጀት ፣ በቡድን ሆኖ ከከተማ ወጣ እያሉ ብርቅና ድንቅ ቦታዎችን መጐብኘትና የመሳሰሉት ልምዶች ቢዳብሩ ጤናማ መዝናኛ ይሆን ነበር ። ታዲያ ይህን በጐ ተግባር ለማስተባበር የግንባሩን ቦታ ማን ይውሰድ ? ’

በራሱ ማቀና ሲጋራ ለመፈለግ ኪሱን ይደባብስ ጀመር ። ትላንት ማታ ሌላ ፣ ዛሬ ጠዋት ሌላ መሆኑ ነው ያማቀው። ' የአንድ ሰው ሁለት መልክ ! ' አለ በልቡ ።

ማቁ ከፊቱ ላይ ሳይጠፋ ሳምሶን ጉልቤው ደረሰ። ፊቱን ጭፍግግ አድርጐታል ። እሱነቱ አስጠልቶት ራሱን የሚጥልበት ቦታ ያጣ ሰው ይመስላል ።

" ታድያስ ? " አለው እስክንድር ፣ ፈገግ እያለ ።

ሳምሶን አፉ መናገር እንዳቃተው ሁሉ ፣ " መቼም አልሞትኩም ! " በማለት ዐይነት አፍንጫውን አጣሞ አንገቱን ወደ ግራ አዘነበለ ። እጆቹን ኪሶቹ ውስጥ እንደ ከተተ ሊቀመጥ ሲል ሱሪው የመተርተር ድምፅ አሰማ ።

" እናትክን ! " አለው ሱሪውን ።

" ጥርሳም እንዳትለው ሱሪው ጥርስ የለው " አለና እስክንድር ቀለደበት ።

ሳምሶን ፈገግም አላለ ። ቢኮረኩሩትም የሚሥቅ አይመስልም ።

" ምነው ደበረህ ? " አለው እስክንድር፣ ማቁን እየሞጠ ። " ምን እባክህ ፣ ነጭናጫ ሴት ነች የገጠመችኝ ። እንዲሁ ስንበጣበጥ ነው ያደርነው ። "

" አይዞህ አንድ ነን ። እኔም ቀዝቃዛ አሮጌት ይገር ነው ያደርኩት ። መጠጥ ምን የማይሠራው አለ ? ብቻ አትፍረድባቸው ። የእንጀራ ጉዳይ ሆኖባቸው ነው እንጂ ሰልችቶአቸዋል ።

" ጥርሳሞች ! ' አላቸው ሳምሶን በልቡ ። ከእስክንድር ጋር መከራከርም መጫወትም አልፈለገም ። መላ ሰውነቱ ደክሞአል ። ለመፍታታት ያህል እንኳ የጠዋት ስፖርት አልሠራም ። ሕይወትን የመሰላቸት ስሜት ተሰማው ። ፊቱን በመስታወት ባያየውም በስሜቱ ጠውልጎ ታየው ። የጠጣበትን ቡና ቤት ፣ ያጠጣውን ገንዘብና አብሯት ያደረችውን ሴት በልቡ እየረገመ ጠረጴዛውን በቡጢ ደበደበ ።

" አቤት ! ምን ልታዘዝ ? " ሲል አሳላፊው ከተፍ አለ ።

" አንድ ጠርሙስ ቀዝቃዛ አምቦ ውሃ ! "

" አዎ ጎሽ ፣ የተቃጠለ አንጀት ለማራስ " አለ እስክንድርም ተደርቦ ።

አምቦ ውሃው ቀርቦላቸው እየጠጡ በመጫወት ላይ ሳሉ ፣ አቤልን በውጭው መስተዋት በኩል አዩት ። ከኋላው የሚያባርሩትን ያህል በፍጥነት ነበር ወደ እነሱ የሚገሰግሰው ። የእስክንድርና የሳምሶን የተደበረ ስሜት አቤልን ሲያዩ ተነቃቃ ። ወሬውን ለመስማት አጠገባቸው እስኪደርስ ተቻኮሉ ። እሱም ከውጭ ሲያያቸው ዐይናቸውን አፍሮ በሆዱ አቀርቅሮ ነበር የተጠጋቸው ። ማታ በቅዠት መልክ የሰማውን " ብር አምባር ሰበረልዎ " አሁን ሁለቱ በውን የሚሉት መሰለው ።

" እህሳ ? ሌሊቱ እንዴት ነበር ? " አለው ሳምሶን ፣ ቀድሞ ሊጨብጠው እጁን እየዘረጋ ።

" ጥሩ ነበር " አለ አቤል ፣ ሁለቱንም ከጨበጣቸው በኋላ ፣ ጠርሙሱ ውስጥ የተረፈውን አምቦ ውሃ በብርጭቆ እየቀዳ ። ጠጥቶ እንደ ጨረሰ በእርካታ ተንፍሶ፣ " እንሒድ እባካችሁ " አላቸው ።

" ቁጭ በልና ተጫወት እንጂ " አለው ሳምሶን ፣ ለወሬው ጓጉቶ ። አቤል ግን መቀመጥ አልፈለገም ። ወደ ካምፓስ ለመሔድ ቸኩሎአል ። በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ አንዳች ነገር ጥሎ ያደረ ይመስል ልቡ ተሰቅሎአል ። እስክንድርም ይህን ስሜቱን ስለ ተረዳለት ለመሔድ ተነሣ ።

ወደ ስድስት ኪሎ ሲጓዙም ሳምሶን ከአቤል የመስማት ጥማቱ እንደ ቀጠለ ነበር ። በዝምታ ትንሽ እንደ ተራመዱ ፣

" ታዲያስ ፣ እንዴት ነበር ? " ሲል ይጠይቀዋል ፣ የሌሊት ተግባሩን አስጐልጉሎ ለማናዘዝ በሚጥር ጥልቅ ስሜት ።

" ደኅና ነበር " ይላል አቤል ፣ ነገሩን ቸል ብሎ ለማሳጠር በሚጥር ስሜት ። ሳምሶን በዚህ መልስ አይረካም ።

" ብርቅነሽ እንዴት ነች ? " ሲል ደግሞ ሊያወጣጣ ይሞክራል ።

" ብርቅነሽ ጥሩ ሴት ነች " ሲል አቤል ነገሩን በአጭሩ ይደመድመዋል ።

አቤል ከብርቅነሽ ጋር ምን ዐይነት የመጀመሪያ ሌሊት እንዳሳለፈ ለመስማት ሳምሶን ብቻ ሳይሆን እስክንድርም ጓጉቶ ነበር ። የብርቅነሽ ጥሬነት ፣ ግልጽነትና ጣፋጭነት ሳያስቡት በሁሉም ልብ ውስጥ ግልጽ ያልሆነ የፍቅር ስሜት አሳድሮባቸው ነበር ። ያም ሆነ ይህ፣ አቤል እንደ ጠበቁት በሰፊው የሚያወራላቸው አልሆነም ። ጓደኞሞች እንዲህ ዐይነት ሌሊት አሳልፈው ጠዋት ሲገናኙ፣ ስለ አዳራቸው ሁኔታ ወይም አብረዋት ስላደሩት ሴት ማውራት የተለመደ ቢሆንም ፣ ለአቤል እንግዳ ነገር ነበር ። ስለ አዳሩ እንዳይናዘዝ የፍሪትና የቁጥብነት ስሜት ኀሊናውን ጨምድዶ ያዘው ።

ብርቅነሽ የትዕግሥትን ቦታ ባትወስድም በአቤል ልብ ውስጥ የተወሰነ ዳርቻ ይዛ ነው ያደረችው ። ለወሲብ የመጀመሪያ ሴቱ በመሆንዋ ብቻም አይደለም ። እስዋም ራስዋ ሁኔታውን በማየትና ሳምሶን የነገራትን በማገናዘብ ለአቤል ቀና ስሜት ስለ ነበራት፣በባነነ ቁጥር አብራው ስትባንን ነው ያደረችው ። የልቧን አጫውታው የልቡን ምስጢር ወስዳለች ። ግልጽነቷና ፍቅራዊ መስተንግዶዋ አስገድዶት አቤልም ስለ ትዕግሥት ሲያጫውታት ነው ያደረው ። የትዕግሥትን ጉዳይ ለብርቅነሽ ግልጽ ማውጣቱ የቆረቆረው ጠዋት ከተለያት በኋላ ነው ። በግትርነት ተወጥሮ የነበረው መንፈሱ እየላላ መምጣቱ ለራሱም ተሰማው ። ምስጢሬ ብሎ ደብቆ የያዘውን የትዕግሥትን ነገር በመጀመሪያ ለሐኪሙ ፣ በትላንቱ ምሽት በመጠጥ ኃይል ለእስክንድር ፣ ሌሊቱን ደግሞ ለብርቅነሽ መናዘዙን ሲያስታውስ፣ የመንፈሱ መላላት ታወቀው ።

ሳምሶንም ሆነ እስክንድር የጓጉትን ያህል ሳያወራላቸው ከዩኒቨርስቲው በር ደረሱ ። ግቢው ጭር ብሎአል ። ፀጥታው ቢሆን ይህ ሰዓት ወደ ትምህርት ክፍል መግ

ቢያ ጊዜ በመሆኑ መራወጥ ይታይበት ነበር።ዛሬ ግን ገና ከእንቅልፉ ያልተነሣም አለ ። የሚነቃነቅ ተማሪ አይታይም ።

እነ አቤል ግቢ ውስጥ ከገቡ በኋላ፣ወደ መኝታ ቤታቸው የሚወስደውን ጠምዛዛ መንገድ ሲይዙ አራት ልጃገረዶች ከሩቅ ተመለከቱ ። ልጃገረዶቹ ሻንጣ ሻንጣቸውን ይዘው ከግቢው በመውጣት ላይ ነበሩ ። ሦስቱ ልጃገረዶች እነማን እንደሆኑ ሦስቱም ወንዶች ከመ ቅጽበት ለዩአቸው ። ትዕግሥት፣ ማርታና ቤተልሔም ነበሩ ። ሁሉም ያላወቋት እንዷ ልጃገረድ የቤተልሔም የመኝታ ክፍል ጓደኛ ነበረች ።

አቤል ደነገጠ ። በአንዴ ገጽታው ተለዋወጠ ። ' ሻንጣ ይዞ ወዴት ነው ? ማርታና ቤተልምሔስ ይሒዱ ፣ ግልግል ነው ። ትዕግሥት ግን እኔን ጥላ ወዴት ነው የምትሔደው? ወደ ቤቷ ወደ ደብረ ዘይት ? አይደረግም ! ' ሲል አሰበ ። ልቡ የድንጋጤ ታምቡር ይመታ ጀመር ።

እስክንድር የአቤልን ሁኔታ ለማጤን ጊዜ አልወሰደበትም ። እነሱን ከነሻንጣቸው ሲያይ ፣ ፈጥኖ የአቤልን ገጽታ ነው የተመለከተው ። ምን ስሜት ሊሰማው እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቃል ። ከልጃገረዶቹ ጋር ፊት ለፊት ያገጣጠማቸውን አጋጣሚ በልቡ ረገመ ። ትንሽ ብንቆይ ወይም ትንሽ ብንቀድም ኖሮ ፣ መንገድ ላይ አንገናኝም ነበር የሚል ከንቱ ጸጸት ተሰማው ። የአገጣጣሚውን መጥፎ ጎን እምብዛም ያላጤነው ሳምሶን ፣ ከልጃገረዶቹ አጠገብ ሲደርሱ ነጻ በሆነ ስሜት ፣ " ታዲያስ ! በጠዋት ወዴት ነው? " አላቸው። ቤተልሔምን ብሎ ነው እንጂ ከትዕግሥትና ማርታ ጋር ንግግር የለውም ።

" እናንተስ በጠዋት ከየት ነው ! " አለች ቤተልሔም፣ ሁሉንም በተራ እየጨበጠች ።

ማርታ ምላሷ አምልጧት ፣ " በረንዳ አድረው ይሆናል ! " ልትል አስባ ለትንሽ መለሰችው ። አቤልን መሐላቸው ማየቷ ነው ያሳፈራት ። ከእነሱ ጋር ደርባ ልትተቸው አልደፈረችም ።

ለተጠየቁት ጥያቄ ከሁለቱም ወገን መልስ የሰጠ የለም ። ነገሩን አደባብሰው የመጨባበጡን ሥነ - ሥርዓት

ያካሒዱ ጀመር ። የእስክንድርና የአቤል ሰላምታ አለዋወጥ ዘዴ የተሞላበት ነበር።እስክንድር በመጀመሪያ ቤተልሔምንና ትዕግሥትን ጨብጦ ማርታን መጨረሻ ያደረገበት ምክንያት አለው ። ከጨበጣት በኋላ እጁን እጅዋ ውስጥ ለማቆየት ፈልጎ ነው ። አቤልም ለተመሳሳይ ምክንያት ትዕግሥትን መጨረሻ ጨበጣት ። ነገር ግን እንኳንስ እጅዋን ይዞ ሊቆይ ቀርቶ፣አንድ አፍታ ዘርግቶ ለመመለሱም ተንቀጥቅጦ ነበር ። ቀና ብሎ ፊቷን ሳያይ ፈንጠር ብሎ ቆመ ። እዚህ አካባቢ ትዕግሥትን በተመሳሳይ ሁኔታ ሲያገኛት ሁለተኛ ጊዜው መሆኑ ነው። እንዴም እንዲሁ ማርታና ቤተልሔም ይዘዋት ወደ ሠርግ ሲሔዱ አጋጥመውት የረገማቸው እዚሁ መውጫ ላይ ነበር ። እና የሁኔታዎች መደጋገም አስደነቀው። እንደ ተቆጣጠረ ሰው መውጪያና መግቢያ ላይ መገናኘቱ አስገረመው ። ‘ እውነትም የፍቅር አምላክ ይኖር ይሆን እንዴ ? ’ ሲል አሰበ ። “ ወይንስ ደግሞ ሳይኮሎጂስቶች ‘ ቴሌፓቲ ’ እና ‘ ክሌርቮያንስ ’ የሚሉት የርቀት ግንኙነት በእርግጥ ለፍቅረኞች ይሠራ ይሆን ? ”

ይህን ጠልቆ ለማሰብ ጊዜ አላገኘም ። አሁን አንገብጋቢው ጥያቄ የትዕግሥት መሔድ ነው ። ለዐሥር ወይም ለዐሥራ አምስት ቀን ተለይታው ልትከርም ? እንዴት ይሆናል ? ያን ሁሉ ቀን ዐይኑ ምን እየተመገበ ይኖራል ?

ቀስ ብሎ አንገቱን አዙሮ ሰርቆ ተመለከታት ። አጠገቧ እንዳይቆም የተከለከለ ይመስል ከጨበጣት በኋላ ፈንጠር ብሎ ፣ ለሁሉም ጀርባውን ሰጥቶአቸው ነበር የቆመው ። አቋቋሙም ሳምሶንና እስክንድር ከሴቶቹ ጋር ያወሩ ስለነበር ፣ እስኪጨርሱ በመጠበቅ ዐይነት ነው ። ሰርቆ ሲያያትና ሰርቃ ስታየው ፣ ድንገት ዐይናቸው ተገጣጠመ ። የሁለቱም ልብ ዘለለ ። እሱ ቀድሞ ዐይኑን ሰበረ ። የሚሆነውን ለማየት ድርቅ ብላ አየችው ። አስተያየቷ ብሽቀትና የመንፈስ መብከንከን ያዘለ ይመስላል ።

ትዕግሥት ራሷ ፣ ከአቤል ጋር ባላት ድፍን ግንኙነት እየበገነች መምጣት ከጀመረች ሰንብታለች ። ሰውን ለሁኔታዎች ተገዥ የሚያደርገው መላመድ መሆኑን ተገንዝባለች ። የአቤልን የዐይን ፍቅር ብትሸሸውም አልሆነላ

ትም ። እሱ ተደብቆ ሳያያት ማደር እንደማይቻለው ሁሉ ፣ እሷም ሳታየው መዋል እንዳቃታት እየተረዳች መጥታለች ። የሚያበግናት የፍቅሩ መልክ - ቢስነት ነው ። መተያየትን ፈልገው ፣ ሲተያዩ መተፋፈር ፤ መገናኘትን ፈልገው ፣ ሲገናኙ መኮሰታተር ፤ እየተዋደዱ መራራቅ ፤ የዚህ አስጨናቂ ሁኔታ መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ብታወጣው ፣ ብታወርደው ፣ ብታሰላስለው ልትደርስበት አልቻለችም ። ሁለቱ የያዙት የማይገናኝ ቀጥታ መንገድ መስሎ ታያት ።

ከዚህ በተጨማሪ የትዕግሥትን ልብ ያቃጠለው የአካባቢው ወሬ ነው ። ባለፈች ባገደመች ቁጥር ከተማሪው ሹክሹክታ መሐል የአቤል ስም ጆሮዋ ውስጥ ጥልቅ ይላል ። ገና ፈተና ከማለቁ ምሽቱን በሴቶች መኝታ ቤት ውስጥ ከምላ ጎደል ሐሜቱ ያተኰረው በእሷና በአቤል ሁኔታ ላይ ነበር ። ሰምታ እንዳልሰማች ጆሮዋን በመድፈን አካባቢውን መጋተር አልቻለችም ። ፈተና ባለቀ ማግሥት ግቢውን ለቅቃ ለመውጣት የተገደደችውም በዚሁ ምክንያት ነው ። ለተወሰኑ ቀናትም ቢሆን ፣ ከአቤል ዐይን መራቁ ለእሷም ከብዷታል ። ሆኖም ማርታና ቤተልሔምም ለዕረፍት ግቢውን ስለሚለቁ ፣ ብቸኝነት እንዳያጠቃት ፈርታ ነው። አብራቸው ግቢውን ለመልቀቅ የወሰነችው ።

“ ትዕግሥት ፣ ምነው ፈዘዝሽ ? ” አላት እስክንድር ፣ ከማርታ ጋር የያዘውን ጨዋታ አቋርጦ ። ከጨበጣት ጀምሮ እጅዋን ሳይለቅ እያዋራት ነበር ። ሳምሶን ጨዋታ አጥቶ “ ታዲያስ ? ” ብሎ እየጠየቀ ፣ “ እና ” ተብሎ እየተመለሰለት ፣ ለወጉ ያህል አብሮአቸው እንደ ቆመ ነበር ።

ትዕግሥት እስክንድር ለጠየቃት ጥያቄ ፣ መልስ ሳትሰጠው ዝም ብላ ተመለከተችው ። አስተያየቷ ጤናማ አልነበረም ። የሦስቱንም ወንዶች የደከመ አካልና የጠወለገ ፊት በማየት ፣ ውጭ አድረው መምጣታቸውን ለመገመት ችላለች ። ግን ውጭ የት ? እና ምን ሲያደርጉ ? ቅናት ተሰማት ። እስክንድር አቤልን እንዳባለገው አድርጋ በመገመት በጥላቻ አየችው ። አቤል በማርታ ላይ ያለውን ዐይነት መጥፎ ስሜት ትዕግሥት በእስክንድር ላይ ማሳየት ጀመረች።

እስክንድር ይህን የትዕግሥትን ውስጣዊ ለውጥ ሳያጤን ፥ “ ማርታና ቤተልሔም እንኳ ከካምፓስ ቢወጡም እዚሁ ከተማ ናቸው ፤ አንቺ ግን የት ልትሔጂ ነው ? ” ብሎ ጠየቃት ።

አቤል የዚህን መልስ ለመስማት ጆሮውን አሰላ ።

ትዕግሥት የእስክንድርን ጥያቄ ለመመለስ ተገደደች ። “እኔም ወደ ሀገሬ ወደ ደብረ ዘይት ነዋ ! ዕረፍቱን ከወላጆቼ ጋር ላሳልፍ ብዬ ነው ። ”

የአቤል ልብ እንደገና ተንፈራገጠ ። ወደ ወላጆቿ ዘንድ ለመሔድ መነሣቷን ገና ሻንጣዋን ሲያይ የገመተ ቢሆንም ፥ ከእሷው አፍ መስማቱ የባሰ ልቡን ረበሸው ። ሆዱን አንቦጫቦጨው ። ደብረ ዘይት ከአዲስ አበባ ስንት ኪሎ ሜትር ይሆን ? በስም እንጂ አቤል ቦታውን አያውቀውም ። እና ቆሞ ሲያሰላስል ትዕግሥትን ሳያይ የሚከርመው ዐሥራ አምስት ቀን፥ዐሥራ አምስት ዓመት መስሎ ታየው።

“ እንሒድ እባካችሁ ! ” የሚለው የሳምሶን ድምፅ አቤልን ከሐሳቡ ፥ እስክንድርንም ከወሬው አቋረጣቸው ። ሆዱን ስለ ሞረሞረው፥ ከሴቶቹ ለመለየት ቸኩሎ ነበር ።

አቤል የሳምሶንን ድምፅ ተከትሎ መራመድ ጀመረ ። ሴቶቹም ለስንብት ዐይናቸውን አቁለጨለጩ ። እስክንድር ግን የያዘውን የማርታን እጅ መልቀቅ አልፈለገም ነበር ።

“ እሺ እንግዲህ ፥ ታዲያ ዕረፍቱን የት ትገኝያለሽ ? ” አላት የግዱን እጅዋን እየለቀቀ ።

“ ደውልልኝ ! ” አለችና ስልክ ቁጥሯን ነገረችው ። ከእሱ ጋር ስታወራ ወደ አቤል እያየች ነበር ። አቤል ሲናገር ወይም ሲጫወት መስማት ትፈልጋለች ። ይህ ጅንን ፥ ኩሩ ሰው ሲተነፍስ ምን እንደሚመስል መስማት ትመኛለች ። ለምን እንደማያናግራት አይገባትም ። አጠገቧ አንድም ቃል ተንፍሶ አያውቅም ። ሲጨብጣትም እጇን እየዘገነነው ነው ። ልክ እንደ አባቴ ገዳይ ነው የሚያያት ።

አሁንም ሳይሰናበታቸው ሔደ ። እስክንድርና ሳምሶን ልጃገረዶቹን ተሰነባብተው ሲከተሉት፥ ኮቴአቸውንና ድምፃቸውን ሰማ ። ከትዕግሥት ጋር ጀርባ ተሰጣጥተው ተለያዩ፥ እሷ ወደ ውጭ ፥ እሱ ወደ ግቢ ። ዝም ብሎ ወደፊት ለመቀጠል አልቻለም ። ዘወር ብሎ ሊመለከታቸው ፈለገ ። እስክንድርና ሳምሶን በአድራጐቱ ሲያፌዙበት በሐሳቡ ታየው። አልዞረም ።

መለየት ! ለጥቂት ቀናትም ቢሆን ከሚወዳት ልጅ ዐይን መራራቅ ! ለዚያውም ሳይሰነባበቱ ፥ ሳይነጋገሩ ፥ የፍቅርን እሳት በልብ ውስጥ አዳፍኖ መለያየት ! ሆዱን ባር ባር አለው ።

ምዕራፍ ሀያሁለት

ጊዜ ወደፊት አይገፈተርም ። ጊዜ ለሰው ጭንቀትም ሆነ ደስታ ደንታ የለውም ። የራሱን ሥርዓት ጠብቆ ነው የሚጓዘው ፤ ያለፈ ጊዜ አይመለስም ፤ የወደፊቱ ደግሞ እንደ ፈለጉት ፈጥኖ አይመጣም ። ሰው በጊዜ ቁጥጥር ሥር ነው እንጂ ፣ ጊዜ በሰው ቁጥጥር ሥር አይደለም ። ሰዓት ሰው ሠራሽ ነገር ነው ፤ ሞላውን በማዞር ካለበት ሰዓት ወይም ደቂቃ ማስቀደም ይቻላል ። የቀን መቁጠሪያም ሰው ሠራሽ ነገር ነው ፤ አንዱን ወር ዐልፎ ሌላውን ወር ማየት ይቻላል ። ቀንን ገፍቶ ማስመሸት ወይም ምሽትን ገፍቶ ማንጋት ግን የማይቻል ነው ።

አቤል ቢቸግረው እንዲህ ዐይነት የጊዜ ምርምር ውስጥ ገባ ። ችግሩ ነው ምርምሩን የጋበዘው ። ቀኑ አልመሽልህ ፣ ሌሊቱ አልነጋልህ እያለው ተቸገረ ። ለሌላው ተማሪ የዕረፍት ጊዜ ፣ ለእሱ ግን የመጨረሻው ደረጃ የጭንቀት ጊዜ ሆኖበታል ። ቀንም ይተኛል ፣ ማታም ይተኛል ። ነገር ግን እንቅልፍ አይወስደውም ። እንዲሁ አልጋው ላይ እየተገላ በጠ በሐሳብ መብከንከን ሆነ ። ጊዜ ከመቼውም ይልቅ የኋሊት እየተጎተተ የሚያቃስት መሰለው ።

ሳምሶን ለዕረፍቱ ወደ ቤቱ ስለ ሔደ መኝታ ክፍላቸው ውስጥ የቀሩት አቤል ፣ እስክንድርና " ድብርት " ብቻ ነበሩ ። " ድብርት " ፈተና ካለቀ በኋላ ፣ ያሳዩው ለውጥ ቢኖር አልጋ ማንጠፉ ብቻ ነው ። በተረፈ እንደ ጥንቱ "ድብርት " ጥናቱም ቢቀር ያው አልጋውን በጋቢ ጋርዶ በራሱ ሕልም ውስጥ መኖሩን አላተወም ። ወደ ውጭም ቢወጣ ብቻውን ነው ።

እስክንድር የዕረፍት ጊዜ ጓደኛው መጽሐፍ ነው ። የአማርኛና የእንግሊዝኛ ልብወለድ መጽሐፎችን እየተዋሰ

ሲያነብ ስለሚውል፣ ቀኑ በፍጥነት ነው የሚገሰግስለት ። ማንበብ ሰልቸት ሲለው፣ወደ መዝናኛው ክበብ እየሔደ ቼስ ይጫወታል ። መቼም ከሱ ቦታ ሰው ቢጠፋ ሚስተር ሆርስ አይጠፉም ።

እስክንድር በዚህ ሁኔታ የዕረፍቱን ጊዜ ቢያሳልፍም፣ ከአቤል ጋር አብሮ መጨነቁ አልቀረለትም ። ዐቅሙ በሚፈቅደው መጠን አቤልን ለማዝናናት የማያደርገው ሙከራ የለም ። ከአነበባቸው መጽሐፎች ውስጥ ጥሩ የሚላቸውን መርጦ ይሰጠዋል ። አቤል ግን ነጻ አዕምሮ ስለሌለው፣ አንዱንም ከነጣዕሙ አንብቦት አያውቅም ። ጀምሮ ሳይጨርስ ሰው ይቀራል ። ወይም በግል ሐሳቡ ውስጥ እየዋዠቀ ገጹን በመቁጠር ብቻ ይጨርሰዋል ። እስክንድር ወደ ቼስ መጫወቻው ቦታ ሲሔድ አቤል አብሮት እንዲሔድ ለማድረግ ቢሞክርም እሺ አላለውም ። ከሚስተር ሆርስ ጋር ከተጣላ ወዲህ የመዝናኛ ክበቡን ረግጦት አያውቅም ።

አቤል ወደ ውጭ ብቅ እያለ ከሰዎች ቢቀላቀል ፣ ጊዜውን መዝናኛ ቦታዎች እየሔደ ቢያሳልፍና በአንዳንድ እንቅስቃሴዎች ቢሳተፍ፣ ጭንቀቱ እንደሚቀልለት እስክንድር ቢረዳም ፣ ይህን ለማድረግ ሁኔታዎች አልተመቻቹለትም ። አብዛኛው መዝናኛ ገንዘብ ይጠይቃል ። ይህን ማሟላት አይችሉም ። ገንዘብ በማይጠይቅበት መዝናኛ ቦታ ለመዋል ደግሞ የአቤል ሙሉ ፈቃደኝነት አይገኝም ። ሌላ ቀርቶ ከእስክንድር ጋር ከሚያወራበት ጊዜ ይልቅ፣ ብቻውን ተደብሮ ውስጥ ውስጡን ነገር ሲያብሰለስል የሚውልበት ጊዜ ይበልጣል ።

ትዕግሥት በተለያየ መልክ በሕልሙ እየመጣች ትታየዋለች ። አንዴ ይጣላሉ ፤ አንዴ ጥላው በመሔዷ የተሰማውን ቅሬታ ይገልጽላታል ፤ አንዳንዴ ደግሞ ደብረ ዘይት ድረስ ሔዶ ሲገናኛት ያድራል ። ቀን ያሰበውን ማታ በሕልሙ ይደግመዋል ። አንዳንዴ በቅዠት ይወራጫል ።

ከትዕግሥት ናፍቆት ጋር ተደርቦ የወላጆቹ ፣ በተለይም የእናቱ ሁኔታ ፊቱ ላይ እየተደቀነበት መጨነቁ አልቀረም ። ያስብ ያስብና ሁሉም ነገር ፍቺ የሌለው እንቆቅልሽ ይሆንበታል ። ሆኖም እንቆቅልሽ ነው ብሎ አይተወውም ።

ተመልሶ በዚያው ሐሳብ ዙሪያ ይሽከረከራል ። በሐሳቡ ከመብከንከኑ ጋር የምግብ ፍላጎቱም እየቀነሰ ስለመጣ በጣም ከስቶ ነበር ። ግን ለዚህ ደንታ አልነበረውም ። አካሉ መንምኖ ነፍሱ ብቻ ከውስጥ ሚን ሚን እስክትል ይጠብቃታል ።

ብርቅነሽ ትዝ ስትለው የደስታ ብርሃን ትፈነጥቃለች ። ስለ እሷ ማሰብ ደስ ይለዋል። አብሯት ካደረ ጀምሮ የመውደድ ስሜት ተቀርጾበታል ። የፍቅሩን ዐይነት ግን በግልጽ ለይቶ ማወቅ አልቻለም ። ትዕግሥትን ይወዳታል ፣ ብርቅነሽንም ይወዳታል ። የመውደዱ ዐይነት ይለያያል ። ሲያስቡት ደስ የሚልና ሲያስቡት የሚያሠቃይ ፍቅር ! ስለ ብርቅነሽ ማሰብ ያስደስተዋል ፤ አያሠቃየውም ፤ ጭንቅላቱን አይበጠብጠውም ። ስለ ትዕግሥት ማሰብ ግን ያሠቃየዋል፣ ይበጠብጠዋል ፤ ያስለቅሰዋል ። እንዲያም ሆኖ ፍቅሩ ለምታሠቃየው ለትዕግሥት ያደላል ። ሙሉ ልቡን ያሳረፈው በትዕግሥት ላይ ነው ። ቀርቦ ምስጢሩን ካካፈላት ፣ ገላዋን ካቀፈውና ትኩሳቷን ሲቀበል ካደራት ሴት ይልቅ፣ ከዕይኑ ላላለፈች ሴት ፍቅሩ ማመዘኑ ለምን እንደሆነ ሊገባው አልቻለም ። ‘ የፍቅር ምስጢሩ ምንድነው ? ’ ሲል አሰበ ፣ ‘ ፍቅር የሚወደው ሥቃይን ይሆን እንዴ ? ’

አንድ ቀን ብርቅነሽን ሲያስታውስ ከውስጡ ፣ “ ሔደህ እያት ” የሚል አንዳች ግፊት መጣበት። ለእስክንድር ሳያማክረው ተደብቆ ብቻውን ሔደ ። ለምን እንደሚሔድና ቢያገኛት ምን እንደሚላት አላሰበበትም። ገብቶ ለመጫወትም ቢሆን ፣ የሚጠጣ ለማዘዝ በኪሱ ገንዘብ የለም ። እናም ቡና ቤቱ አጠገብ ሲደርስ ቀጥ ብሎ ቆመ ።

የቡና ቤቱ በር ክፍት ነው ። ነገር ግን ድምፅ አይሰማበትም ። እንደዚያ ዕለቱ ምሽት ሙዚቃና የሰው ጫጫታ የለበትም ። ከዘንቦች እምምታ በቀር ጸጥ ረጭ ብሏል ። መግባት አልደፈረም ። እየተንጎራደደ ሰው ብቅ እስኪል ይጠብቅ ጀመር ። ጥቂት እንደ ቆየ፣ አንዲት ሴት የከሰል ምድጃ ይዛ ከውስጥ ብቅ አለች ። አለባበሷ ግድየለሽ ነው ። ሻሿን የገርዳሳ አስራለች ።

አቤል ሲያያት ክው አለ ። የዋህነቷንና ጥሬነቷን ልይታ የቡና ቤቷ ባለቤት ማታ ማታ እንደ አሻሻጭ ፣ ቀን ደግሞ እንደ ገረድ ነው የምትጠቀምባት ። ከሰሉ እንዲቀጣጠልላት ምድጃውን ወደ ንፋስ አድርጋ ቀና ስትል አየችው ። ቶሎ አልለየችውም ። ያው እንደ መንገደኛ ነበር የተመለከተችው ። ስታየው ተደናግጦ ጀርባውን ስጥቷት ወደ ኋላው ሊመለስ ፈልጎ ነበር ። ግን ዐይኑን ከማሸሹ በፊት የምታውቀው ወንድ መሆኑን ለይታ ጥርሷን ብልጭ አረገችለት ። እሷን ፍለጋ ያልመጣ ለመምሰል እጁን ኪሱ ከትቶ በግዴለሽ አረማመድ ተጠጋት ። ስሜቱን ለመሸፈን በከንቱ ደከመ እንጂ በድንጋጤ ፊቱ ቀልቶ ገንባሩን አልቦት ነበር ።

“ ውይ ፣ አንተ ነህ እንዴ ? በሞትኩት ! ምነው ጠፋህ ? ” አለችው ፣ ከልብ በሆነ አነጋገር ።

ምንም ሳይመልስላት ፣ ስሜቱን በፈገግታ ብልጭታ ለመሸፈን እየሞከረ ጨበጣት ።

“ ሙት ፣ እውነቴን እኮ ነው ፤ ጠፋህ ? ቆይ እስኪ ስንት ቀን ሆነን ፣ አዎ ፣ ሳምንት ዐልፎሃል ። እኔ ከዛሬ ነገ ትመጣለህ እያልኩ በልቤ ሳስብህ ነበር ” አለችው ።

‘ እውነቷን ይሆን እንዴ ? ’ ሲል አሰበ ። ግን አሁንም ከመቅለስለስና ራሱን ከማከክ ሌላ ምንም አልመለሰም ። ድምጿ የእውነት ቅላጼ ነበረው ። የተናገረችው የልቧን ነው ፤ ለአቤል አንድ ጥሩ የሆነ ስሜት አድሮበታል ። ሴት ያልለመደ መሆኑና የተማረ መሆኑ ፣ በስሜቷ ውስጥ እንዲቀረጽ አድርጎታል ። እናም እንዳለችው አብራው ካደረችበት ሌሊት በኋላ ዐልፎ ዐልፎ በልቧ ታስበው ነበር ። የተሠማራችበት ሙያ ሆነና በወሲብ ተገናኙ እንጂ ፣ እሷ ለሱ ያደረባት ስሜት ሐሳቧንና ችግሯን እንደምታዋየው ፣ እሱም በዕውቀቱ እንደሚረዳት የቅርብ ዘመድ ወይም ታናሽ ወንድሟ ዐይነት ነበር ።

“ በል እሺ ግባ ! በር ላይ አትቁም ” አለችው ፣ ከእሱ አንዳችም ቃል ባለመስማቷ እያዘነች ።

“ አአይ ልሒድ ፤ ድንገት ሳልፍ'ኮ ነው ” አላት ፣ በአንድ በኩል እንደ መግደርደር እያለ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኪሱን ባዶነት እያሰበ ።

“ ግባ እባክህ ፣ ትንሽ ተጫውተህ ትሔዳለህ ” አለችና ጎተት አደረገችው ።

በባዶ እምነትና ኩራት የተገነባ ግትር ሰውነቱን አቅልላ መጎተቷ ውስጡን ደስ አሰኘው ። ራሱን አቅልሎ መቅረብ አይችልም ። ንጹሕ ልብ ያለው ሰው አቅልሎ ሲቀበለው ግን ይወዳል ። በልቡ “ የሚቀጥለውስ ደረጃ ምን ይሆን ? ” እያለ ያለማመንታት ወደ ውስጥ ዘለቀ ።

“ ምንም ሰው የለም እንዴ ? ” አላት ፣ ቅርቡ ባጋጠመው ወንበር ላይ እየተቀመጠ ።

“ ውይ ፣ ቀን ምን ገበያ አለ ብለህ ነው ? ያው ማታ ነው ሞቅ የሚለው ” አለችው ፣ አጠገቡ እየተቀመጠች ።

አጠገቡ ስትቀመጥ ጊዜ ፣ ልቡ ናድ ናድ ይል ጀመር ። ለሰውነቷ መቅረቡን ቢወደውም ከእሷ ካልመጣ በቀር ፣ እሱ ደፍሮ መጠጋጋት ወይም መተሻሸት አልቻለም ። እንዲያውም በዚያን ሌሊት ራሱ ደፍሮ ክንዱን ዘርግቶ ይህችን ሴት አቅፎ ማደሩን ዛሬ ተጠራጠረ ። ማድረግ በማይችሉት ነገር ላይ ለመገፋፋት መጠጥ መልካም ቅመም ሳይኖረው አይቀርም ብሎ ገመተ ።

“ እሺ ፣ እስቲ በል ተጫወታ ” አለችው ቀጠለችና ፣ ሣቅ እያለች ።

እሺታውን ለመግለጽ የሚዋትቱት ዐይኖቹ ከጥርሷ ጉራማይሌ ንቅሳት ላይ ዐረፉ ። የሣቋ ምንጭ ምን እንደሆን ማወቅ አልቻለም ። ‘ ምናልባት አብሬአት ያደርኩባትን ሌሊት አስታውሳ ይሆን እንዴ ? ’ በሚል ጥርጣሬ በአንዴ ፊቱን ሳብ አስመጠው ።

“ አሁን ዕረፍት ላይ ናችሁ አይደል ? ” አለችው ፣ ስሜቱን ሳታጤን ።

" እዎ ፣ ብቻ ዕረፍቱ ወደ ማለቁ ነው ።"

" ጨካኝ ነህ ግን አንተ ። ዕረፍት ሆነህ ይህን ያህል ቀን ሳትመጣ ? ! "

" ጭካኔ አይደለም " አላት ፣ ድምፁ ከመድከሙ የተነሣ የራሱ መሆኑ እያጠራጠረው ።

" ታዲያ ምንድነው ? "

ምን እንደሚላት ግራ ገባው ። ፍርሀት ፣ የኪስ መድረቅ ? ወይስ ጭራሹን ያለ መፈለግ ?

ለመልሱ ሲጨነቅ አይታ፣ ሐሳቧ ቶሎ ሌላ ነገር ላይ ሮጠ ።

" ያቺ ልጅ እንዴት ናት ? "

" የቷ ? " አለ ፣ የማይፈልገው ጥያቄ መሆኑን ገምቶ ዐይኑን እያፈጠጠ ።

" ያቺ ዩኒቨርስቲ ያለችው ! ያንን ሌሊት ያጫወትከኝ " አለችው ደንታ ባጣ ቀላል ስሜት ።

ከሌላ ሰው ስለ ትዕግሥት አንዳችም ጥያቄ ሆነ ጨዋታ ህነሣበት አይወድም ። የብርቅነሽ አጠያየቅ ግን፣ ለጊዜው ቢያስደነግጠውም ድንጋጤው ጭንቅላቱ ውስጥ አልቆየም ። ምክንያቱም የብርቅነሽ አጠያየቅና አቀራረብ እንደ ምሁራኑ ከፍተኛ አትኩሮት ያለውና የሰው ስሜት የሚያጤን ዐይነት አልነበረም ። ነገሮችን ሁሉ ቀላል አድርጋ በቀላል አነጋገር ነው የምታቀርባቸው ። መልስ ብታገኝ አገኘች ፣ ባታገኝም ወደ ሌላ ጨዋታ ትሸጋገራለች እንጂ ፣ ሥራዬ ብላ የሰው ስሜት በማጥናት ወይም ነገር በማውጣጣት አትጨነቅም ።

"ግቢ ውስጥ የለችም ፤ ለዕረፍቱ ወጥታለች " አላት ፣ ደፋር ጥያቄዋ አደፋፍሮት ፣ ድንጋጤው ተግ ብሎለትና ነገሩን ማቅለሏ ፣ እሱም አቅልሎ እንዲያየው ገፋፍቶት ።

" ውይ ፣ ሠፈሯ የት ነው ? " አለችው ።

" ደብረ ዘይት " ሲላት፣ ጉሮሮው ላይ አንዳች ነገር እየተናነቀው ነበር ።

" ውይ ፣ ከአዲስ አበባ ውጭ ? " አለችው ከልቧ አዝና ። ትዕግሥትን ሳያያት ማደር እንደማይችል አጫውቷት ስለ ነበር፣ ርቃው ስትከርም ምን ያህል እንደሚሠቃይ በመገመት አዘነችለት ። ከእሱ መልስ ሳትጠብቅ ቀጥላ ፣

" ስትሔድ ምን አለችህ ? " አለችው ።

" ምንም ። "

" ምንም አልተባባላችሁ ? አሃ ፣ በቃ ተነጋግራችሁ አታውቁም ? "

በአሉታ ራሱን ነቀነቀ ።

" ውይ ! ምን ዐይነት ፍቅር ነው ? " አለች ።

" ጭፍን ፍቅር ነዋ ! " አላት በብሽቀት ። የሆነ ነገር ዐይኑን ለበለበው ። የገዛ ልቡ ከበደው ። በዚህ አርዕስት ላይ ቀጥሎ ከብርቅነሽ ጋር መጫወት እንደማይችል ገመተ ። ይህን ያህልም ግልጽ የሆነው ለእሷ ብቻ ነው ። እሷም ከዚያ በላይ ልትጠይቀው አልቻለችም ። ቃላት መለዋወጥ ቀርቶ በሙሉ ዐይን ተያይተው ከማያውቁ ፍቅረኞች ምን መረጃ ይገኛል ? አብዛኛውን ድፍን ሁኔታ አብረው ያደሩ ዕለት አጫውቷታል ። እና ዝም ብላ ዐይን ዐይኑን ስታየው፣ስሜቱ የተጋባባት ትመስል ነበር ።

እንዲህ እየተጫወቱ ትንሽ እንደ ቆዩ፣የቡና ቤቷ ባለቤት ከጓዳ ብቅ አለች ። ከቀኑ አምስት ሰዓት ተኩል አካባቢ ቢሆንም እሷ ገና በሌሊት ልብሷ ነበረች ። ፊቷ ሲያዩት ይከብዳል ። በዚያ ላይ ገና ከመኝታዋ መነሣቷ ስለሆነ ፊቷ ላይ የተጋደመው ሰምበር መልክ አሳጥቶአታል ። በሒና የቀላው ጸጉሯ ትንሽ ባያደምቃት ኖሮ፣ ጭራ ትመስል ነበር ። አቤል ያን ምሽት ያያት ሴት መሆኗን ተጠራጠረ ። ያኔ ታምር ነበር ። ' የቡና ቤት ሴቶች ውበታቸው ማታ ማታ ብቻ ነው ማለት ነው ? ' ሲል አሰበ ።

" ባለቤቷ ናቸው እንዴ ? " ሲል ብርቅነሽን ሹክ ብሎ ጠየቃት ።

" አዎ " አለችና ብርቅነሽ እየሣቀች ፥ " ብቻ እንትቱ ስትላት እንዳትሰማህ ፥ አትወድም " አለችው ፥ እሷም እንደሱ ሹክ ብላ ።

" እኝህን የሚያክሉ ሴትዮ እንቺ ማለት ነውር ነው ብዬ ነው ! "

" ሆሆይ ! እሷ ስትሰነብት ልጃገረድ ነኝ ሳትል አትቀርም " አለችው ፥ እንደገና ሣቋን አፍና ።

ባለቤትየዋ እየቀረበች ስትመጣ ጨዋታቸውን አቋረጡ ።

" ከሰሉ አልተቀጣጠለም እንዴ ? " ስትል ብርቅነሽን በተቆጣ ድምፅ ጠየቀቻት ። ቡና ማፍያቸው ሰዓት ነበር ።

" ውይ ፥ ኧረ እስካሁን ይቀጣጠላል " አለችና ብርቅነሽ ተስፈንጥራ ብድግ አለች ። ከሰሉ እንዲቀጣጠል ውጭ ማድረጓን ዘንግታው ነበር ።

" ቫሸሸ ሊወድቅ ነው ? " አላት አቤል ፥ ከጸጉሯ ላይ ሲንሸራተት አይቶ ።

" ኬሬዳሽ ! " አለችና ጭራሹን ፈትታ ጣለችው ። በልቡ ' የዋህ ፍጡር ' እያለ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ ውጭ ተከተላት ።

" ምነው ተጫወት እንጂ ፥ እኔ 'ኮ ከሰሉን ላገባ ነው ። "

" ተጫወትኩ 'ኮ ! ልሒድ " አላት ፥ ወደ ፊቱ እየተራመደ ።

" እሺ በል ፥ ማታ ትመጣለህ ? "

" እ ? "

" ማታ ና ! "

እሺ ብሎ ተሰናበታት ። ደስ ብሎት ዋለ ። እናም ' እንዲህ ደስታ የምትሰጠኝ ከሆነ ለምን ደጋግሜ አላያትም ? ' የሚል ሐሳብ አደረበት ። ብርቅነሽ ጋ መሔዱን ለእስክንድር አልነገረውም ። ድብርትን ፈልጎ አንድ ብር እንዲያበድረው ጠየቀው ። ድብርት ምን ጊዜም ገንዘብ አያጣም ። ለክፉ ቀን በሚል እምነት እንደሚቀብር አቤል ያውቃል ። ከዚያ በፊት ጠይቆት ስለማያውቅ ፥ ድብርት ገርሞት አንድ ብር አወጣና ሰጠው ። ከሳጥኑ ውስጥ ፥ ከሥር ፥ ከመጽሐፍ ሽፋን ብሩን መዝዞ ሲያወጣ ሲያየው አቤል ገረመው ። ' የሰውን እጅ ብቻ ሳይሆን የራሱንም እጅ ሳይጠረጥር አይቀርም ' አለ በሐሳቡ ።

አቤል ኮካ ኮላውን ይዞ ማታ ወደ ብርቅነሽ ዘንድ አመራ ። ከምፓስ ውስጥም ሆነ ውጭ እስክንድር እንዳያገኘው መንገድ እየመረጠ ነበር የሔደው ።

እቡና ቤቱ ሲደርስ የተለመደች ፍርሀቱ መጣችበትና ቆሞ ትንሽ አመነታ ። ቡና ቤቱ ጢም ብሎ ሞልቶ ፥ ቻቻታው ደርቶ ነበር ። ቀስ ብሎ ወደ በሩ ተጠጋ ። አንገቱን ወደ ውስጥ ገባ ሲያደርግ ፥ ዐይኑ አነጣጥሮ ብርቅነሽ ላይ ዐረፈ ። የሆነ ነገር ፊቱ ላይ ብልጭ አለበት ። ራሱን መቆጣጠር ያቃተው ይመስል - በሩን ደገፍ ብሎ ቆመ ። ብርቅነሽ ባንኮኒው አጠገብ አንድ ወንድ ጭን ላይ ተቀምጣ ቢራ ትጠጣለች ። ከት ከት እያለች ከልቧ ትሥቃለች ፥ ትጫወታለች ። የዋህ ልቧን ለማንም ከፍታ ትሰጣለች ። ወንድየው በአንድ እጁ ወገቧን ደግፎ በአንደኛው ጡቶቿን እያሻሸ አብሯት ይሥቃል ፤ ይጠጣል ፤ ይጫወታል ።

አቤል እንዳያት እንድታየው አልፈለገም ። ለምን ከማንም ጋር ትሥቃለች ? ለምን ከማንም ጋር ትጫወታለች ? ለምን ለማንም ልቧን ትከፍታለች ? ሳታየው ቀስ ብሎ ወደ ኋላው ተመለሰ ።

ወደ መንገዱ ሲያቀና በሐሳቡ የቡና ቤቱ ሰው ሁሉ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ፥ " ግባ እንጂ ፥ ምነው ተመለስክ ? የቀናህባት ሴት አለች እንዴ ? ቡና ቤት 'ኮ ነው የመጣኸው " የሚለው መሰለው ።

የገዛስሜቱን እንደሚሸሽ ሁሉ ፊቱን ወደ ስድስት ኪሎ አቅንቶ መንገዱን ጀመረ ። በሐሳቡ ውስጥ ገንዘብ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ አብሮት ገሰገሰ ። ገንዘብ ፈለገ ። ገንዘብ ፈጥኖ ለማግኘት ጓጓ ። ገንዘብ የነገሮች ሁሉ ማሰሪያ ነው ፤ አለ በልቡ ።

ምዕራፍ ሀያምስት

የዕረፍቱ ጊዜ ለአቤል ብቻ ሳይሆን፥ለአብዛኛው ተማሪ ረዥም ነበር ። በጥናት መወጠር የለመደ አእምሮ ሥራ ሲፈታ ደቂቃዋም ትረዝማለች ። የአዲስ አበባዎቹ ተማሪዎች እንኳ አብዛኛዎቹ ወደየዘመዶቻቸው ወጥተው ስንብተዋል።ከየክፍለ ሀገሩ የመጡ ተማሪዎች ግን፥ መሔጃም ሆነ ጊዜ ማሳለፊያ በማጣት በዝነው ነው የሰነበቱት ። ቀን ቀን ሁሌም ተደብረው ይውላሉ ። ጨዋታና ቀልድ የሚኖረው ማታ ማታ በየመኝታቸው ሲሰፍሩ ነው ። በአብዛኛው መኝታ ክፍል ተደጋጋሚ የጨዋታ አርዕስቶች ሆነው የሚቀርቡት የአቤልና የትዕግሥት የዐይን ፍቅር ፥ የለማና የቤተልሔም ጉዳይ ፥ ወይም ሌሎችን የተደረሰባቸው አዲስ ፍቅረኞችን ማጋለጥ የመሳሰሉት ናቸው ።

የግቢውን የፍቅር ታሪክ መሰለልን መዝናኛቸው አድርገው የያዙ አንዳንድ ተማሪዎች አሉ ። ወሬአቸውን የሚያደምቁት የፍቅረኞቹ ጓደኛ በመምሰል ቀርበው ምስጢራቸውን እየሰረሰሩ ነው ። በዚሁ ተግባራቸው ፥ “ ሳተላይት ” “ ሮይተር ” ፥ “ ቢቢሲ ” የሚል የቅጽል ስም የወጣላቸው ተማሪዎች ነበሩ ። ወሬ አጠናቅረው መጥተው በግቢው ያሰራጯሉ ። ምሽት ላይ እነሱ ሲመጡ፥ ሁሉም ወሬ ለመስማት ከተኛበት ብድግ ብድግ ይላል ።

“ ያልሰማህ ስማ ! የሰማህ ላልሰማ አሰማ ! አዲስ ዜና :— በዚህ በዝግ ጊዜ ውስጥ አንድ መምህር ከአንዲት ተማሪው ጋር በዋቢ ሸበሌ ሆቴል የዳንስ ምሽት ላይ መታየቱ፥ ከታመኑ የዜና ምንጮች ደርሶናል ። ”

‘ ደሞ ማን ይሆን ? ’ እያለ ተሜ ከመኝታው ውስጥ በአንሶላው ብቻ እየወጣ ፥ በጆሮው ሳይሆን በመላ ሰውነቱ የሚያዳምጥ ይመስል፥ ወሬው ወደ ነፈሰበት ይጠጋል ።ምን

ጌዜም የሚሞቀው ፣ እነ “ ሮይተር ” እነ “ ሳተላይት ” ያሉበት መኝታ ክፍል ነው ። ብዙ ተማሪ ክፍሉን ትቶ እነሱ ያሉበት ድረስ እየመጣ ያመሻል ።

“ ማነው እሱ በናትህ ? ”

“ ለማን ታውቋታላችሁ ? ሁለተኛ ዓመቶችን የሚያ ስተምር ራስ - በራ ሰውዬ ። ”

“ እ ፣ ዐወቅኩት ። ከማን ጋር ነው የታየው ? ” ይላል የሚያውቀው ።

ለማን የማያውቀው ደግሞ ፣ በእዝነ ልቡናው ለማን ፍለጋ ይኳዃል ።

“ ቤተልሔም ከምትባል ቀይ ወፍራም የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ጋር ... ”

“ ውይ ! እሷንማ ሲያወጣት ቆይቶ የለም እንዴ ? ” ይላል ፣ ከአሁን በፊት ቀድሞ ወሬውን የሰማ ።

“ ሒ ... ድ ? ” ይላል ፣ ለወሬው እንግዳ የሆነ ሁሉ በአድናቆት ።

“ ኧረ እንዲያውም ሊጋቡ ነው ” ሲል ቤተልሔም ጣት ላይ የጌጥ ቀለበት ያየው ደግሞ ነገሩን ያጋንናል ።

“ ስጥ እንግዲህ ! ” ይላሉ ፣ ውሾቱ አልዋጥላችሁ ያላቸው ።

“ ተወው እስኪ ያውራ ፣ እጅሬ መቼም መስጠት ልማዱ ነው ። ”

ውሸት ፈጥረው የወሬ ማጣፈጫ እያደረጉ በማቅረብ የተካኑ ተማሪዎች አሉ ። “ ስጥ እንግዲህ ” የጨዋታቸው አርዕስት ሲሆን ፣ እነሱ ደግሞ “ አባ መስጠት ” በመባል ይታወቃሉ ።

ውሸቱ ከፍ ያለ እንደሆነ “ ሮግጫ ” ይባላል ። ዋሾዎቹ “ ረጋጮች ” ሲባሉ ፣ የፕሮግራማቸው ስም ደግሞ

“ረገጣ” ነው ። ማኅበራዊ ኑሮን የሚጠሉ ጥቂት መሠሪዎች ካልሆኑ በስተቀር ፣ የአብዛኛው ተማሪ — የሮይተሩም ፣ የረጋጩም — ተግባር የዩኒቨርስቲውን የዕረፍት ጊዜ ሕይወት ለማጣፈጥ ነው ።

“ እባካችሁ ጨዋታውን ወደ ቀልድ አትቀይሩት ፣ ” ይላል ለወሬው የጓጓ ፣ አምርሮ ።

“ በቃ ፣ ይኸው ነው ።ለማ ቤተልሔምን አወጣት ። ”

“ ‘A’ ያለምንም መጨነቅ በእጅዋ ገባ ማለት ነው ። ከጆሴ ደግሞ ከራሱ ትምህርት ዐልፎ ሌሎቹም ጓደኞቹ እንዲረዷት ይለምንላታል ። ”

“ እናታቸውን ! እነዚህ ሴቶች ጨረሱን ’ ኮ ! ጭንቅላት ሲያጡ በወሲብ ዩኒቨርስቲን ሊወጡ ! ” ሲል ፣ ሁሉም በብሽቀት ጥርሱን እያንቀጫቀጨ በጅምላ ሴቶቹን ይራገማል ።

“ ለካ ለዚህ ነው ” ይላል ፣ አርዕስቱ እንዳይቋረጥ የሚፈልገው ፣ ለአርዕስቱ እንደገና ሕይወት ለመስጠት ቅመም እያዘጋጀ ።

“ ምኑ ? ” — ብዙ ጆሮዎች ሰልተው ይቆማሉ ።

“ ሰሞኑን ለማ ከሚስተር ራህማን ጋር ግንባር ፈጥሮ የሚታየው ! ”

“ ራህማን ? ”

“ ሚስተር ራህማን እኛያ ህንዳዊው ። ”

“ እ ! እ ! ” — ሞቅ ያለ ሣቅ ።

“ ለማ የቅርብ ጓደኛቸው ሆኗል ። ለሻይ ሲወጡም አንድ ላይ ነው ። ”

“ የዓላማ አንድነት ነዋ ያስተሳሰራቸው ። ”

“ እሳቸው’ኮ ሐኪም ሳያዝላቸው አይቀርም ። በሴት ቀልድ አያውቁም ፤ በተለይ ወፍራም ሴት ሲወዱ ! ”

" ብቻ እንድ፯ቀን ቤት ጭን ውስጥ ትንፋሽቸው ቆሞ እንዳይገኙ " ይላል የበሸቀው ክፍል እያፌዘ ።

ጨዋታው ይቀጥልና ከመምህራን ተመልሶ ወደ ግል መበሻሸቅ ያመራል ። እርስ በርስ መጋለጥ ይመጣል ። እንዱ የሌላውን ምስጢር ለመጎልጎል በነገር ጎሸም ያረጋል ። ነገሩ የሚነካው ቁስለኛ ካለ ፣ በወዲሁ ማኩረፍ ይጀምራል ። ሆኖም እነ " ሮይተር " የማንም ኩርፊያ አያግዳቸውም ።

" ነገርን ነገር ያነሣዋል " ሲሉ ይጀምራሉ ።

" ደሞ ምን ልታመጡ ነው ? "

" የቤተልሔምን ጓደኛ ለ የወጣ የሞከረው ከመሐላ ችንም አይጠፋም 'ኮ ! "

" ማንን ? ያቺን ማርታን እንዳይሆን ? ! "

" እህሳ ! "

ማርታ ፣ ዐይኗ ስለማያርፍ ሳይሆን አይቀርም ፤ ብዙ ተማሪዎች ዐይናቸውን ጥለውባታል ። በግቢው ውስጥ ከብዙ ሴቶች መሃል ተለይታ ትታወቃለች ። ጠይቀው ሊያወጧት የሞከሩ ፣ ወይም የሚፈልጓት ከእስክንድር ሌላ ብዙ ናቸው ። በአለባበሷ ድምቃ ከመታየቷ ሌላ ፣ ምን ጊዜም ዐይኗ አያርፍም ። ስትበላ የአዳራሹን ወንድ እየቃኘች ነው ። ስታጠናም መጻሕፍት ቤት የተቀመጠ ፍጥረት አይቀራትም ። ወንዶችን ብቻ ሳይሆን ሴቶችንም ሥራዬ ብላ ነው የምታየው ። ሴቶችን የምታየው ግን በጤናማ ዐይን አይደለም ። ዘወር ብላ እንደ ሽንኩርት ትልጣቸዋለች ። በተለይ ደመቅ ያለች ሴት ማርታ ዐይን ውስጥ ከገባችማ አለቀላት ! ውሽት ፈጥራ ስሟን ታጠፋለች ። !

" ውይ ! ያቺን ሞጥሟጣ ነው እንዴ ? " ሲል ቁስል ያለበት ማጥላላት ይጀምራል ።

"ሞጥሟጣነቷን በምን ዐወቅከ ? " በማለት ፣ ሳታላይቶቹ ያፌጣሉ ።

" ደሞ ምን ልታመጡ ነው ? እዚያው በጸበላችሁ ! " ቁስለኛ ማኩረፍ ይጀምራል ።

" አንተ ምን አስኮረፈህ ? አንድ ቀን ብቻ ነው የጠየቅካት ። እና 'F' ኮሙኩመህ ተመለስክ ። ይሄ ደሞ አያሳፍርም ። "

ጠይቆ ሲሳካ 'A' እንደማግኘት ሲቆጠር ፣ ሳይሳካ ሲቀር ደግሞ 'F' መኮምኮም ይባላል ።

" አይ አጅሬ ! መኮምኮም አይስለቸው ! " በማለት ከፊሉ ያጃንቃል ።

" ስጡ እንግዲህ ! አባ መስጠቶች መስጠት አይሰለቻችሁ ። "

" ምኑ ላይ ነው ውሽቱ ? "

" መዋሸት ብቻ ነው እንዴ ! ደኅና አርጎ መርገጥ ነው እንጂ ። ምን ታረጉ ? ! ዝም ብለው የሚረገጡላችሁ አገኛችሁ ፤ ርገጡዋቸው ! "

" አስረጅ ! " በማለት ከመሐል ነገሩን አጠናካሪ ይናገራል ።

" ደሞ አንተ ምን ልትል ነው ? "

" አጅሬ አንድ ቀን፣ እነማርታ የሚያጠኑበት አካባቢ ያለ ሥራው ሲያንዣብብ አግኝቼዋለሁ ። "

አጥቂ ሲበዛበት ቁስለኛው የሚያመልጥበትን ዘዴ ያሰላስላል ። ኩርፊያ አያዋጣም ። ቁጣም አያዋጣም ። የዚህ ዐይነት አዝማሚያ ከታየ ተማሪዎቹ የባሰ ያሳብዳሉ ። ያለው ምርጫ ቀስ ብሎ በዘዴ አርዕስት ማስለወጥ ነው ።

" ይልቅ የሚገርመው የዚያች የእነ ማርታ ጓደኛ ነገር ነው ። ያ የአራተኛ ዓመት የማዕረግ ተማሪ የሚወዳት ! " ሲል እንደ ምንም ወደ ሌላ አርዕስት ይሸጋገራል ።

የቤተልሔም እና የማርታ ነገር ከተነሣ የትዕግሥትም አይቀርም ። ብዙ ጊዜ አብረው ስለሚታዩ ነው ። አቤል ከሚ

ሉተር ሞርስ ጋር ተጣልቶ የአዕምሮ መታከሚያ ሆስፒታል ከተወሰደ ጊዜ ጀምሮ እነ “ ሮይተር ” ስለዚህ ጉዳይ በቂ መረጃ አላቸው ።

“ ትዕግሥትን ነው እንዴ ? ምስኪን ፍጥረት ! እሷ'ኮ ምንም አታውቅ ። ከድንግሏ እንደምትገኝ እኔ በዐሥር ጣቴ እፈርማለሁ ። ”

“ በምን አወቅክ ? የፈተንካት አትመስልም ? ! ”

“ ኧረ ግፍ አትናገሩ ! እሷ ከቀለም ሌላ ምንም አታውቅ ዐይኑ - ውሃዋም ያስታውቃል ። ”

“ አትመን እባክህ ፣ ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች እንደሚባለው ነው ። ከእኔ ማርታ ጋር ውላ ደሞ ጤነኛ ትሁን እንዴ ? ! ” ሲል ጠርጣሪው ክፍል መከላከያውን ይደረድራል ።

እነ “ ሳተላይት ” እዚህ ላይ ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት ሙግቱን ያስረዳሉ ።

“ እሷስ ገና ጥሬ ናት ። ምን ያረጋል ! ጥሬነቷ ነው ያንን ጂኒየስ ልጅ ያሳበደው ። ”

“ ማንን ? ”

“ አቤልን ነዋ ! ”

“ ምስኪኖች ! የእነሱ ነገር በጣም ይገርማል 'ኮ ! በዐይን ከመተያየት በስተቀር ተቀራርበው ተነጋግረው አያውቁም ።

“ የዐይን ፍቅር ነዋ ! ዐይኑካ ! ”

“ ግን በምን ጣለበት ? ሌላ ሴት'ኮ ቀና ብሎ አያይም ። ”

“ የዐይን ፍቅር ላይ የጣለው ጭምትነቱ ሳይሆን አይቀርም'ኮ ! ” በማለት የራሱን አስተያየት አከል የሚያደርግም አይጠፋም ።

“ ምን ዋጋ አለው ! ጮማ ጭንቅላት ይዞ አሁን በሷ ምክንያት መቀወሱ ነው ። እንዴ'ኮ አዳራሹ ውስጥ ከነምግቡ የወደቀው እሷን እሷን ሲያይ ነው ! ”

“ ትቀልዳለህ ? ይህን ያህል ? ”

“ አንተ ደሞ ለዚህ ለቀላሉ ጉዳይ ነው እንዴ ? ዕብዶች ሐኪም ቤት ድረስ ገብቷል 'ኮ ! ”

“ በእሷው ምክንያት ? ” ይላል ፣ ቀድሞ ነገሩን የሰማውም እብሮ ። ያልሰማው ጓጉቶ ነው ፤ የሰማው ደግሞ የሌላውን የፍቅር ሥቃይ ደጋግሞ መስማቱ ስለሚጥመው ነው ።

“ ታዲያስ ! እንዲያውም እንደ ሰማሁት ከሆነ ፣ ዘንድሮ ትምህርቱን ጨርሶ የሚመረቅ አይመስልም ። ”

“ ያሳዝናል ! ” ሲል አብዛኛው ከንፈሩን ይመጣል ።

“ ምን ያሳዝናል ፣ ያናድዳል እንጂ ! ዱዳ አይደል ። ቀርቦ አያናግራትም ! ? እምቢ ብትለውም ሴት አልጠፋ ባገሩ ! ” የሚል ተሚጋች ከመሐል ብቅ ይላል ።

“ እንደሱ አትበል እባክህ ፣ አያድርስ ነው ፤ ፍቅር መልኩ ብዙ ስለሆነ መፍረድ አትችልም ። ”

ግማሹ በኀዘኔታ ፣ ግማሹ በቀልድ ፣ የጦፈ ክርክር ያካሒዳል። አጋጣሚ ሆኖ እስክንድር ጨዋታቸው መሐል ካለ፣ ኮቴውን ሳያሰማ ቀስ ብሎ ሹልክ ይላል ። የአቤልን ከቶ መስማት አይፈልግም ። እሱ ለአቤል ያለውን ቅርበትና ጓደኝነት ብዙዎቹ ስለሚያውቁ ፣ በጨዋታው ላይ የበኩሉን መረጃ እንዲሰጣቸው ዐይን ዐይኑን ሲያዩት ነው የሚሾልከው ።

ሳምሶን ጉልቤው በዕረፍቱ ጊዜ ካምፓስ ውስጥ አለመኖሩ ነው እንጂ ፣ በአቤል ጉዳይ ከስንቱ ጋር በተጣላ ነበር። በግቢው የአቤልና የትዕግሥት የዐይን ፍቅር የጨዋታ ማድመቂያ ሆኗል ። የሚወራው እውነትም ቢሆን ሳምሶን የአቤልን ስሜት የሚጎዳ ነገር እንዲነሣ አይፈልግም ።

እስክንድር በግቢው ውስጥ በሚካሔዱት የመዝናኛ ቀልዶች ፣ ተረቦችና ጨዋታዎች በተሳተፈ ቁጥር አንድ የሚገርመው ነገር አለ ። አብዛኛው ወሬ ስለ ሴትና ወንድ ግንኙነት ወይም ስለ ፍቅር ነው ። ‘ ሌላ ወሬ አጥተን ነው ፣ ወይስ ዕድሜአችን ነው በዚህ አርዕስት ዙሪያ የሚያሽከረክረን ? ወይስ ደግሞ የጋራ ስሜታችንን የሚነካ ጉዳይ ይህ ብቻ ሆኖ ነው ? ’ ሲል ያስባል ። ነገር ግን ከእቻው ጋር በተገናኘ ቁጥር ዞሮ ዞሮ አመርቂ አርዕስት ሴት ትሆናለች ፤ እና የዕድሜን ኃይል ግለት ይታዘባል ። ትኩስ ፣ እፍላ ፣ የሚያቅበጠብጥ ዕድሜ

የዕረፍቱ የጨዋታ ምሽቶች ከፍቅር እልፍ ያሉ እንደሆን ፣ በግቢው ውስጥ ከሚታዩት ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያርፋሉ ። የፍቅር ጉድጓድ እንደሚሰረስሩት ፣ “ሮይተሮች ” ሁሉ ፣ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ፀረ መጤ ሃይማኖት አቋም ይዘው እያንዳንዷን እንቅስቃሴ እየተከታተሉ የሚተርቡም አሉ ። በየዕለቱ በየትኛው ድርጅት ውስጥ ማን እንደ ተመለመለ ወሬው አያመልጣቸውም ። ሌላው ቀርቶ የትኛው የሃይማኖት ድርጅት በግቢው ውስጥ የአባላት ብዛት እንዳለው የሚያውቁና በአሀዝ የሚያቀርቡ አሉ ።

“ ስሞኑን ‘ ሁለተኛው አምላክ ’ ታላቅ ኪሳራ ደርሶበታል ” ሲል አንዱ ይጀምራል ።

“ እንዴት ? ”

“ በፈተና ሰሞን የመለመላቸው አባላት አብዛኛዎቹ ፈተና ካለቀ በኋላ ፣ ርግፍ አርገው ትተውታል ። ከመብላታቸው በፊት መጸለይ አቁመዋል ። አስረጅ ! ”

“ በዩኒቨርስቲው ውስጥ በሃይማኖት አባልነት የተመለመሉት የሚታወቁት ፣ ምግብ አዳራሽ ውስጥ ከመመገባቸው በፊት አቀርቅረው ሲጸልዩ ነው ። ጸሎቱን ሲያቆሙ ኮንትራታቸውን መጨረሳቸው ይታወቃል ። ”

“ አትለኝም ! ማን ማን ተወ በናትህ ? ”

የሚታወቁትን በስም ፣ የማይታወቁትን በመልክ ጥቆማ ይኳሔዳል ።

“ ምነው ውጤት እስኪቀበሉ እንኳ ቢቆዩ ፤ ፈተና ላይ ‘ የረዳቸው ’ አምላክ የኢራሚውንም መምህር እጅ በማሳሳት እንዲረዳቸው ። ”

“ ቸኮሉዋ ! ምን ያርጉ ፣ በዕረፍት ጊዜያቸው በሃይማኖቱ ከቀጠሉበት ሴቶቹ መደነስ ፣ ወንዶቹም መጠጣት ሊያመልጣቸው ሆነ — ለማን ጀቴ ብለው ! ”

“ አሥቂኝ ነው ? ” ይላል አንዱ ቀልደኛ ከመሐል ።

“ እንዴት ? ” ሲል ሁሉም ጆሮውን ይቀስራል ።

“ ከአምላካቸው ጋር ድብብቆሽ ጨዋታ ነው ’ ኮ የተያያዙት ። ፈተና ሲደርስ ይሰግዱለታል ። ከፈተና ከወጡ በኋላ ይዘጉታል ። ዋ ብቻ አንድ ቀን ያመረረ ዕለት ! ”

ቀልዱ ሲኮረኩራቸው መሣቅ እየፈለጉ በልባቸው አፍነው የሚያሳልፉ አሉ ። ሲሥቁበት አምላክ እንዳያያቸው የፈሩ ይመስላሉ ። አንዳንዱ በዚህ አርዕስት ላይ ሲያሾፍ ፣ ሲቀልድ ፣ ሲተርክ ፣ አንዳንዱ ደግሞ ገለልተኛ ሆኖ መስማቱን ይመርጣል ። ጨዋታውን ማዳመጥ ይወዳል ፤ ግን በሃይማኖታዊ ድርጅቶችም ሆነ በአምላክ ላይ አንዳችም ተቃርኖ አያነሣም ። “ ከአፍ የወጣ እንጂ በጆሮ የገባ አያረክስም” ከሚል ግምት ላይ የደረሰ ይመስላል ። አፌን በዳቦ ነው ነገሩ ።

እንዲህ ዐይነቶቹ የጨዋታ ምሽቶች በብዙ ተማሪዎች አእምሮ ተቀርጸው የሚቆዩ ናቸው ። በሴቶችም መኝታ ክፍል ቢሆን ፣ ሐሜቱና ተረቡ ቢበዛ እንጅ አያንስም ። ወንዶችን በማብጠልጠል ፣ አስተማሪዎችን በመቦጨቅና ራስን በመካብ ሴቶቹን የሚያህል የለም ። “ እገሌ ‘ኮ እንድወጣለት ጠይቆኝ ዘጋሁት —! ያ ባላገር ! ” የብዙዎቹ የጋራ ፈሊጥ ይመስላል ። የሚገርመው ደግሞ ሴቶቹ ሲዋሹ እርስበርሳቸው ይቻቻላሉ ። እንደ ወንዶቹ “ረገጣ” እና “ስጥ እንግዲህ ” እየተባባሉ ቅስም አይሰባበሩም ።

ቀልድ እየፈጠሩና ወሬ እያጠናቀሩ ተማሪውን የሚያዝናኑትን ያህል ፣ በየአስተማሪው ቢሮ እየተሹለከለኩ የፈተና

ውጤት ከመነገሩ በፊት መርዶ የሚያረዱ አንዳንድ ተማሪ ዎችም አሉ ። እነዚህን ማንም አይወዳቸውም ። የዩኒቨርስቲ ሕይወታቸው ዕድሜ የሚኖረው ለአስተማሪዎች ወሬ በማ መላለስ ነው እየተባሉ ይታማሉ ። ማርክ ቀድሞ የመስማት ሱስ አለባቸው ። የራሳቸውን ሳይሆን የሌሎቹንም የመስማት ሱስ ነው የያዛቸው ። እወደድ ባይ ወይም ለተራ ወሬ ጆሮ ውን የሰጠ መምህር የሦስት ልጆችን ማርክ ይነግራቸዋል ። እነሱ ደግሞ አባዝተውት የሃምሳ ልጆችን ውጤት እንደ ሰሙ አርገው ወሬውን ይዘራሉ ። መምህሩ ፣ " ወደቀ " ካላቸው እነሱ ፣ " ተሰበረ " ብለው በግቢው ውስጥ ሽብር ይፈጥራሉ ።

" ዘንድሮ ይህን ያህል ፍሬሽ ይባረራል " ብለው በአፋቸው ሙሉ ሲናገሩ ፣ የሬጂስተራሩን ቢሮ የያዙት ይመስላሉ ።

" የእንትን አስተማሪ ከዚያ ሁሉ ተማሪ መሐል ሁለት 'A' ብቻ ነው የሰጠው " ሲሉ የመምህሩ የቅርብ ጓደኛ ይመስላሉ ።

ከመልካም ዜና ይልቅ የዝቅተኛና የውድቀት ማርክ ሽብር መፍጠር ነው የሚቀናቸው ። ሌላውን አስበርግገው እነሱ የወሬ ሱሳቸውን ካልተወጡ አይሆንላቸውም ።

እቅጩ የሚታወቀው ግን ጊዜው ደርሶ ማንኛውም ተማሪ የራሱ ውጤት በራሱ እጅ ከደረሰው በኋላ ነው፡።

አቤል ከሁሉም ርቋል ። ጥሩውንም መጥፎውንም አይሰማም ። " ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው ፤ " እንዲሉ ፣ በሱ ላይ የሚወራብትን አያውቅም ። ነገር ግን ተማሪው ሁሉ በሽ ታውን ያወቀበት እየመሰለው ከሁሉም ሸሽቶአል ። ጓደ ኛው ብቸኝነቱ ነው ። አጫዋቹ የቀን ቅዠቱ ፣ የሌሊት ሕልሙ ነው ። ሌላው ክፍል ተማሪው ተሰብስቦ እያወራ ፣ እየቀለደና እየተጫወተ ሲሟሟቅ ፣ አቤል ከብቸኝነቱ ጋር ይሟገታል ። ትዕግሥትን ያልማል ፤ በል ሲለውም ይረግ ማታል ። የመልካሙ ተበጀን ዘፈን ያዜማል ። ብርቅነሽን ያስባል ። ከራሱ ጋር ይሥቃል ። ከራሱ ጋር እየተጣላ ያለ ቅሳል ።

በዚህ ዓይነት የሚገፉ ዐሥራ አምስት የዕረፍት ቀናት የዐሥራ አምስት ዓመት ያህል ቢረዝሙም ማለቃቸው አይቀርም ፤ ያልቃሉ ። የሚጠበቀውም ቀን መድረሱ አይቀርም ፤ ይደርሳል ።